# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 162 የካቲት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# “አፍሪካውያን ልዩነቶቻችንን ያለማንም ጣልቃ ገብነት መፍታት ይኖርብናል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ ፡- አፍሪካውያን ልዩነቶቻችንን ያለማንም ጣልቃ ገብነት መፍታት ይኖርብናል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ገለጹ። ኢትዮጵያ “ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ” በሚለው መርህ እንደምትቀጥልም አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በ36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ እንደገለጹት፤ አፍሪካውያን አባቶች ችግሮችን ለመፍታት ይጠቀሙባቸው የነበሩ እውቀቶችን እንተገብራለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ላይ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደፊት በአፍሪካ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ተፈጥሯዊ እንደሆኑና መፍትሄው ከውስጥ መሆን አለበት ማለታቸውን በንግግራቸው አንስተዋል።

ኢትዮጵያ “ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ” የሚለውን መርህ እንደምትከተል ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በሶማሊያ እና ደቡብ ሱዳን በመሳሰሉ ሀገራት በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ያላትን ተሳትፎ እና ከኤርትራ ጋር የተደረሰውን የሰላም ስምምነት በማሳያነት ጠቅሰዋል።

በኢኮኖሚው ረገድም ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ አፍሪካን ለመመገብ የሚያስችላትን ስራ በግብርናው ዘርፍ አጠናክራ እየሰራች ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ኢትዮጵያ በምግብ ራስን ለመቻል ባለፉት አራት ዓመታት የግብርናውን ምርታማነት ለማሳደግ በአነስተኛ ግብርና የተሰማሩ አርሶ አደሮችን በክላስተር

“አፍሪካውያን ልዩነቶቻችንን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - እዮብ ተፈራ




ECCS
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# ለአፍሪካ ሰላምና ልማት መረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት እንደሚደግፍ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ገለጸ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ኅብረት የአህጉሪቱን ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ በሚያደርገው ጥረት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ድጋፍ እንደሚያደርግ ዋና ጸሀፊው አንቶኒዮ ጉተሬዝ ገለጹ፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ትናንት በአዲስ አበባ በተጀመረው 36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ የአፍሪካን የልማት ሂደት መደገፉን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ አፍሪካ ሽብርተኝነትን በመዋጋት፣ ሰላምን በማስፈንና ኢኮኖሚ ለማሳደግ በምታደርገው ጥረት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አብሮ ይሰራል፡፡

ለአፍሪካ ሰላምና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ‹‹ለአፍሪካ ዕድገት የተሻለ የምለውን ለመስራት ቁርጠኛ ነኝ››

- አዛሊ ኡስማኒ
አዲሱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርና የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ድምጽ በዓለም አደባባይ ተደማጭ እንዲሆንና የተሻለች አህጉር ለመፍጠር የምችለውን ሁሉ ለመስራት ቁርጠኛ ነኝ ሲሉ አዲሱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርና የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት አዛሊ ኡስማኒ ገለጹ፡፡ ኮሞሮስ የ2023 አፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርነትን ከሴኔጋል በይፋ ተረከባለች።

36ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ በህብረቱ ዋና መቀመጫ አዲስ አበባ ትናንት ሲጀምር ሊቀመንበርነቱን ከሴኔጋል ፕሬዚዳንት ማኪሳል የተቀበሉት የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት አዛሊ ኡስማኒ፤ ‹‹ለኮሞሮስ ይህ ትልቅ ታሪካዊ እድል ነው፡፡ ይህን ዕድል በመጠቀም ለአፍሪካ የተሻለውንና የሚበጃትን ለመስራት

‹‹ለአፍሪካ ዕድገት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# “በትግራይ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ሁሉን አሳታፊ ሲሆን ይገባል”

- አረጋዊ በርሔ (ዶክተር)
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር

ገጽ 4



## "የአሁኑ ትውልድ የኢትዮጵያን አንድነት ሊጠብቅ የሚችለው ያለፈ ታሪኩን በአግባቡ ሲገነዘብ ነው"

**-ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን
የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የአሁኑ ትውልድ የሀገሩን አንድነት ሊያስጠብቅና የነገይቷን ኢትዮጵያ በጋራ መገንባት የሚችለው ያለፈው ታሪኩንና ማንነቱን በአግባቡ ሲገነዘብ ነው ሲሉ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ተናገሩ:: ተተኪው ትውልድ የሀገሩን ታሪክ፣ባህል መመርምሮ ሊያውቅ ይገባል ብለዋል::

ልጅ ዳንኤል ዛሬ የሚከበረውን 86ኛው የአርበኞች መታሰቢያ ቀን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤የአሁኑ ትውልድ የሀገሩን አንድነት ሊያስጠብቅና የነገይቷን ኢትዮጵያ በጋራ መገንባት የሚችለው ያለፈው ታሪኩንና ማንነቱን በአግባቡ ሲገነዘብ ነው::

ዛሬ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በኩራት አንገቱን ቀና አድርጎ እንዲኖር የደምና በአጥንት ዋጋ ተከፍሎለታል፤ ጀግኖች አርበኞች ለአሁኑ ትውልድ ዘመን የማይሽረው ውስጣዊ ጥንካሬን በደምና አጥንታቸው ገንብተውልን አልፈዋል፤የአሁኑ ትውልድም የሃገሩን አንድነትና ልማት ለማስቀጠል ተግቶ መስራት ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል::

በየጊዜው ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ታሪኳን ለማበላሸት ጎንበስ ቀና የሚሉ የውጭ አካላት እኩይ ተግባሮቻቸው እንዳይሳካ አርበኞች አባቶቻችን ያስቀመጡልን አሻራ ትልቅ መሆኑን ያስታወሱት ልጅ ዳንኤል፤ ጥንታዊያን አርበኞች ለሀገር ክብርና ለነጻነታቸው የከፈሉትን መስዋዕትነት የሚዘከርበትና ተተኪው ትውልድ የሀገሩን ታሪክ እየተማረ በሄደ ቁጥር ለሀገሩ ክብር እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ የበዓሉ ታስቦ መዋል የሀገር ፍቅር ስሜት ለማዳበርና ለአንድነት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል::

በዚህ ረገድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና የመገናኛ ብዙሃን ግንዛቤ በማስጨበጥና ትክክለኛ መረጃ በማሰራጨት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አመላክተዋል::

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ የሰማዕታት ቀን በጣም ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ነው። በሶስት ቀን ብቻ ከ33 ሺ በላይ ሰዎች ለሀገራቸው ብለው በፋሽሽት ጣሊያን በግፍ እንደ ቅጠል የረገፉበት ነው፤ እኛም ከዚህ ትምህርት ወስደን አንድነታችን ልናጠናክር ይገባል::

የማህበሩ ፕሬዚዳንት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ መታሰቢያው የተለያዩ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎችና በርካታ ሕዝብ በተገኘበት በስድስት ኪሎ ሰማዕታት ሐውልት ስር የአበባ ጉንጉን በማስቀመጥና የተለያዩ አባቶችን የሚዘክሩ ስነ-ስርዓቶች በማከናወን በድምቀት ይከበራል::

ከሰማዕታት ሐውልት ጋር ያለው መርሃ- ግብር እንደተጠናቀቀ ወደ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጉዞ ከተደረገ በኋላ ለሰማዕታቱ ጸሎተ ፍትሀት ተደርጎ የጀግኖች አርበኞች አጥንት ያረፈበት ቦታ ላይ የአበባ ጉንጉን ይቀመጣል ብለዋል::

# በ2014/15 የምርት ዘመን

## 6 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ተሰበሰበ

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በ2014/15 የምርት ዘመን ስድስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት መሰብሰብ መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። የሩዝ ምርትን በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ውጭ ለመላክ እየተሰራ መሆኑም ተመላክቷል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ልማት ድህረ ምርት ባለሙያ ወይዘሮ ድንቅነሽ አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014/15 ምርት ዘመን በተለያዩ ክልሎች 178 ሺህ 183 ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ ምርት ለምቷል። በዚህም 2014/15 የምርት ዘመን ስድስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የሩዝ ምርት ተሰብስቧል፡፡

በተለይም በኦሮሚያ፣አማራ፣ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም በጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የሩዝ ምርት በብዛት የለማባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን ወይዘሮ ድንቅነሽ ጠቅሰዋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቀጣይ 10 ዓመት ውስጥ በትኩረት ሊሰሩ ከሚገባቸው ስራዎች ተብለው ከተለዩ ክንውኖች መካከል አንዱ የሩዝ ምርታማነት ማሻሻል ነው ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ድንቅነሽ ገለጻ፤ ለሩዝ ምርታማነት የሚረዳ ስትራቴጂ እና ሃገራዊ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል። የሩዝ ሰብል ምርታማነትን ለማሳደግ በመስኖ ጭምር ማልማት እንደሚገባ አቅጣጫ ተይዞም ወደ ስራ ተገብቷል። ከውጭ የሚገባውን የሩዝ ምርት በአገር ውስጥ ለመተካትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አበረታች ጅማሮዎች እየታዩ መሆኑን አስረድተዋል።

በ2013/14 የምርት ዘመን 87 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኖ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ሩዝ መሰብሰቡን ጠቁመው፤ በ2014/15 የምርት ዘመን ግን የማልማት አቅሙ ከእጥፍ በላይ በማደጉ 178 ሺህ 183 ሺህ ሄክታር የመሬት ስፋት በሩዝ ምርት መሸፈኑን ገልጸዋል።

የሩዝ ምርታማነትን በዘላቂነት በማሳደግ በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ውጭ ለመላክ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ምርታማነቱን ለማሳደግ በሚደረግ ጥረት ለሩዝ ምርት ግብዓት የሚውል የተለያዩ የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና፣ የግብርና መሳሪያዎች ለአርሶ አደሩ ካለፉት ጊዜያት በተሻለ መልኩ እንዲቀርብ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የሩዝ አመራረት አዲስ ለሆነባቸው አካባቢዎች አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ የተሻለ ምርት ማግኘት የሚችልባቸውን አሰራሮች የማስተዋወቅ ስራም እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በሩዝ ሰብል ምርት ላይ የሚሳተፉ ባለሃብቶች ሚና ወሳኝነት አለው ያሉት ወይዘሮ ድንቅነሽ፤ በሜካናይዜሽን በታገዘ አሰራር በሚያከናውኑት ልማት ለአርሶ አደሩም ተሞክሮ የሚሆን ስራ ማከናወን እንደሚቻል ገልጸዋል።

በሩዝ ምርት የሚሳተፉ የግል አልሚዎች ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ የሚረዳ ስርዓት ተዘርግቷል፤ በቀጣይም ኢንቨስተሮች በሩዝ ምርታማነት ላይ በጋራ መስራት የሚችሉበት አማራጭ እንዳለ ጠቁመዋል።



# በመዲናዋ አንድ ነጥብ 2 ሚሊዮን የቤት ፍላጎት አለ

## -ፍላጎትን ለማሟላት ሦስት አማራጮች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንድ ነጥብ 2 ሚሊዮን የቤት ፈላጊዎች መኖራቸውን የ10 ዓመቱ የቤት ፍላጎት ጥናት እንደሚያሳይና የቤት ፍላጎትን ለማሟላት ሶስት ተጨማሪ አማራጮች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የኮንትራት አስተዳደር ባለሙያ አቶ ሙሉጌታ ጉደታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ከፍተኛ የሆነ የቤት ፍላጎት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ ሶስት አዲስ አማራጮች ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

መንግስት የሚያስገነባቸው የተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ከቤት ልማት አማራጮቹ መካከል አንደኛው መሆኑን ጠቁመው፤ ከተማ አስተዳደሩ በግንባታ ዘርፍ ከሚሳተፉ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን እያስገነባቸው ይገኛል ብለዋል።

በመዲናዋ የሚገነቡ ተገጣጣሚ ቤቶችን የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ማስጀመራቸውና ግንባታቸው እየተፋጠነ መሆኑ ተገልጿል። የተገጣጣሚ ቤቶቹ ግንባታ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በአካባቢ ልማት ምክንያት ተነሽ ለሚሆኑ ግለሰቦች፣ በመካከለኛና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚተላለፉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለኪራይ የሚሆኑ ቤቶች እንደሚገነቡ ጨምረው የገለጹት አቶ ሙሉጌታ፤ በመጀመሪያው ዙር በተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ አምስት ሺህ ቤቶች እየተገነቡ መሆኑን አስረድተዋል።

በጎ ፍቃደኞችን በመጠቀም የሚሰሩ ግንባታዎች የቤት ፍላጎቱን ለማሟላት ተግባራዊ ከተደረጉት አማራጮች መካከል ሁለተኛው መሆኑን አመልክተው፤ የችግረኛ ቤቶችን በመለየት በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ የቤት እድሳት ማድረግና ተጨማሪ እድሳት የሚፈልጉ ቤቶችን የመለየት ስራ መስራት የሚያስችል አማራጭ ነው ብለዋል፡፡

በዚህም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን እና አቅመ ደካማዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በየክፍለ ከተሞቹ ላይ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አቶ ሙሉጌታ ጠቁመዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ተግባራዊ የሚደረገው ሶስተኛው አማራጭ የግልና የመንግስትን አጋርነት በመጠቀም የሚከናወን የቤት ልማት ነው። አልሚዎች በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት የራሳቸውንና የመንግስትን ድርሻ ወጪ ሸፍነው ግንባታዎችን ይገነባሉ። ከዚያም አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች እንዲተላለፍ የሚያደርግ አማራጭ ተዘጋጅቷል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ ሙሉጌታ ገለጻ፤ የቤት ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ አስተዳደሩ ከጋራ መኖሪያ ቤቶች ልማት በዘለለ የተለያዩ ችግር ፈቺ ስራዎችን አቅም በፈቀደ መልኩ እያከናወነ ይገኛል። በመዲናዋ በ10 ዓመት እቅድ የቤት ፍላጎት በተጠና ጥናት መሰረት 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን የቤት ፍላጎት መኖሩ ተረጋግጧል።

ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በተከናወኑ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ ላይ ከ600 ሺህ በላይ ሰዎች ተመዝግበዋል፤ ቀሪው ደግሞ ሌሎች አማራጮች ላይ የተመዘገቡ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ግንባታ አማራጭ ለማስፋት 10/90፣ ከ20/80 እና ከ40/60 በተጨማሪ በቅርቡ 70/30 የተሰኘ የቤት ልማት ተጀምሯል።

በ14ኛው ዙር የ20/80 እና 3ኛው ዙር የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ የማውጣት ሥነ-ሥርዓት በህዳር ወር 2015 ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን፤ በድምሩ ዕጣ የወጣላቸው 25 ሺህ 791 የቤት ዕድለኞች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ውል እየተዋዋሉ መሆኑ ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አፍሪካውያን ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚሆኑ ማህበራዊ እሴቶች ባለቤት ናቸው!

የትኛውም ማኅበረሰብ በራሱ ማዕቀፍ ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ የሚሆን በቂ ተፈጥሯዊ አቅም አለው። ትልቁ ችግር ይህን አቅም አውቆ በአግባቡና በኃላፊነት መንፈስ ፣ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ የሚያስችል ተነሳሽነት/ፍላጎት የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ነው። ወደ ራስ ማየት አለመቻል፤ ከዚህም ተነስቶ ለራስ በቂ ክብር መስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ መሰረት አለማዋቀር ግን ይህንን አቅም በተፈለገው መጠን ሥራ ላይ እንዳይውል ያደርጋል።

ይህ ችግር በተለይም ባለንበት ዘመን፤ሁለንተናዊ ጣልቃ ገብነት በስፋት ጎልቶ በሚታይበት፤ የተለያዩ ማኅበረሰቦችን ጨምሮ ሀገራትን ፣ አህጉራትን እና ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ሳይቀር ከፍያለ ዋጋ እስከፈለ ይገኛል። ችግሩ በአግባቡ ሊገራ ካልቻለ በቀጣይም ያለመረጋጋት እና ሁከት ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው።

ችግሩ በተለይ በአፍሪካውያን ላይ ጎልቶ የሚታይ ነው። አፍሪካውያኑ አንድም የችግሮቻቸውን እውነተኛ ምንጭ በአግባቡ ካለማስተዋል፤ ከዛም በላይ ለችግሮቻቸው መፍትሄ አድርገው የሚወስዷቸው የውጪ የመፍትሄ ሃሳቦች "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆነውባቸው ከነጻነት ማግስት ጀምሮ ያሳለፏቸው ስድስት አስርት ዓመታት በአብዛኛው ያለመረጋጋትና የሁከት አመታት እንዲሆኑ አድርጎባቸዋል።

በርግጥ አፍሪካውያን በዘመናት መካከል በትውልዶች ቅብብሎሽ ያካበቷቸው፤ እጅግ ብዙ የችግር /የግጭት ማስወገጃ ባህላዊ እሴቶች ባለቤቶች ናቸው። ዘመናትን ተሻግረው መምጣት የቻሉትም በእነዚሁ አቅሞች ነው። በነጻነት ትግሉ ወቅትም እነዚህ እሴቶች የነበራቸው አስተዋጽኦም የማይተካ እንደነበር ይታወሳል።

ከነጻነት ዋዜማ ጀምሮ በአፍሪካውያን ምሁራን የተጀመረው የፓን - አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴም ቢሆን የነዚህን እሴቶች የማይተካ ዋጋ በአግባቡ በመረዳት ላይ የተመሰረተ፤የአህጉሪቱን ሕዝቦች ቀጣይ እጣ ፈንታ ብሩህ ለማድረግ ሊኖራቸው የሚችለውን የላቀ ጠቀሜታ ከግምት ያስገባ ነው። አስተሳሰቡ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በብዙ ፈተናዎች ለማለፍ የተገደደውም ከዚሁ የተነሳ እንደሆነ ይታመናል።

ዛሬ ላይ አፍሪካውያን ስለነገዎቹ ትውልዶቻቸው እጣ ፈንታ ሲያስቡም፤ ከሁሉም በላይ ጥላ ሆኖ የሚያሳስባቸው፤ በውስጥ ጉዳዮቻቸው ላይ የሚደረጉ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶችና ጣልቃ ገብነቶቹ የሚፈጥሯቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች እና ሁኔታዎቹን ለመቀልበስ የሚከፈለው ውድ ዋጋ ነው።

ይህ ከነጻነት ማግስት ጀምሮ አፍሪካውያኑ በራሳቸው እጣ ፈንታ ላይ ለመወሰን አቅም ያሳጣቸው የውጪ ጣልቃ ገብነት በራሱ የችግሮቻቸውም ምንጭ መሆኑ ለችግሮቻቸው ግዝፈት ዋነኛ አቅም ከመሆን አልፎ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚደረገው ጥረት ፈታኝ እንዲሆን አድርጎታል።

አፍሪካውያኑ አንድም የችግሮቻቸው ዋነኛ ባለቤት አለመሆናቸው፤ ከዚያም በላይ የተፈጠሩ ችግሮችንም በራሳቸው አቅም እንዲፈቱ ዕድሉን መነፈጋቸው፤ ያልዘሩትን የመከራ ዘር እንዲያጭዱ ባልተገባ መልኩ ተፈርዶባቸው ከፍ ያለ ዋጋ ለመክፈል ተገድደዋል።

ከዚህ ከትውልድ ትውልድ እየተሻገረ የመጣን ችግር ለዘለቄታ ለመፍታት ከሁሉም በላይ አፍሪካውያን ለችግሮቻቸው መፍትሄ ከማፈላለግ በፊት የችግሩን እውነተኛ ምንጭ አጥርተው ሊያውቁት ያስፈልጋል። ከእነርሱ በላይ ስለችግሮቻቸው ሊያስብ የሚችል ኃይል ሊኖር እንደማይችል ከቀደመው አሳዛኝ ታሪክ ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል።

የአህጉሪቱ ሕዝቦች የፖለቲካ ነጻነታቸውን ለመቀናጀት ያጋጠማቸው ተግዳሮትና ተግዳሮቱን አሸንፎ ለመሻገር የከፈሉት መስዋእትነት፤ የፖለቲካ ነጻነቱን ሙሉ ለማድረግ ላለፉት ስድስት አስርቶች ያጋጠሟቸው ፈተናዎች እና ፈተናዎቹ እያስከፈሏቸው ያለው ዋጋ ከእነርሱ በላይ ስለነሱ ሊያስብላቸው የሚችል ላለመኖሩ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

አፍሪካውያን ከቀደመው ታሪካቸው ሆነ ከነጻነት ዋዜማ ጀምሮ ይዘዋቸው ከተነሷቸው በራስ የመተማመን መንፈስ አንጻር ለራሳቸው ችግሮች መፍትሄ ሆነው የመቆም ትልቅ አቅም ባለቤቶች ናቸው። ይህ ደግሞ በነጻነት ትግሉ ወቅት የተፈጠሩ ፈተናዎችን በአሸናፊነት ተሻግሮ ለማለፍ ወሳኝ አቅም ሆኗቸው ታይቷል።

በዚህ ወቅትም "ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ" በሚል የአህጉሪቱ ሕዝቦች በአዲስ መንፈስና መነቃቃት ቃላቸውን ከፍ አድርገው የሚያሰሙት ከዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት ነው። በርግጥም እውነታው ከዚህ የተለየ አይደለም፤ ችግሩን ማንም ስለ ምንም ይፍጠረው አፍሪካውያን የትኞቹንም ችግሮች አሸንፈው መሻገር የሚያስችሉ ታላላቅ ማኅበራዊ እሴቶች ባለቤቶች ናቸው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስአፍሪካውያን መጻኢ ተስፋ...

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የአፍሪካ ህብረት መመስረት ዘመናትን በባርነት ቀንበርና በድህነት ላሳለፉት የአፍሪካ ሀገራት የነጻነትንና የእድገትን ጭላንጭል የከፈተ ነው። ምንም እንኳን ህብረቱ ከተመሰረተበት አላማና ሊሰራ ከሚገባው አንጻር ሲመዘን በርካታ የቤት ስራዎች የሚቀሩት ቢሆንም የአውሮፓውያንን ተጽእኖ ከመቋቋም ጀምሮ በፖለቲካውም በኢኮኖሚውም መስክ የተመዘገቡት ውጤቶች አበረታች ነበሩ።

ይህም ሆኖ ዛሬም ድረስ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት እምቅ የተፈጥሮ ሀብታቸውን ተሸክመው በርካታ አምራች ወጣቶችን ይዘው ውስብስብ በሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጠላልፈው ይገኛሉ። ይህም ህብረቱ በቀጣይ እነዚህን ችግሮች ለዘለቄታው ለመፍታት ብዙ ስራዎች መስራት እንዲጠበቅበት አድርገውታል።

የአፍሪካ ሀገራት አሁን ላሉበት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች የውጪ ሀይሎች ጣልቃ ገብነት ዋነኛ ችግር ነው። ችግሩ ከሁሉም በላይ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ አንድነታቸውን አጠንክረው እንዳይጓዙ አድርጓቸዋል። ህብረቱም የታሰበው ያህል ውጤታማ ሆኖ ለአህጉሪቱ ህዝቦች የተሻለ እድል መፍጠር አልቻለም።

ህብረቱ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ በዘለቀ ጉዞው የሰራቸው በርካታ ተግባራት ቢኖሩም ፤ በተለይም የአህጉሪቱን ህዝቦች በኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዘርፎች በማስተሳሰር፤ በአለም አቀፍ መድረኮች ተሰሚነታቸውን ለማሳደግ ገና ብዙ መስራት ይኖርበታል፡፡ በዚህ በኩል ያጋጠሙት ሆነ እያጋጠሙት ያሉ ተግዳሮቶች በቀጣይም ፈተና እንደሚሆኑበት፤ ለዚህ ደግሞ በአህጉሪቱ ሀገራት መካከል ሊኖር የሚገባውን የእርስ በእርስ ግንኙነት መጠናከር ፤ ይህንንም ከግብ ለማድረስ ህብረቱ ጠንካራና ተከታታይነት ያለው ስራ መስራት ይጠበቅበታል ።

አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት በእርስ በእርስ ግጭቶች ውስጥ አመታት እያስቆጠሩ ይገኛሉ። በዚህም ህዝቦቻቸው እየከፈሉት ያለው ዋጋ ከፍ ያለና ነገዎቻቸውን በተስፋ እንዳይጠብቁ ፈተና ጭምር ሆኖባቸዋል። ለዚህም ሁነኛ ማሳያ ልትሆን የምትችለውን የቅርብ ጎረቤታችን ሱማሊያን እንመልከት። በሀገሪቱ አመታት ያስቆጠረ የእርስ በእርስ ግጭት አለ ፤ ግጭቱ ሀገሪቱን የአሸባሪ መፈንጫ አድርጓል ፤ የችግሩ ጦስ ለጎረቤት ሀገራትም ተርፏል።

የደቡብ ሱዳን ጉዳይም ከዚሁ የራቀ አይደለም። በእነዚህ ሀገራት ያለውን ችግር ለመቅረፍ ከአፍሪካ ሀገራት ሰላም እንዲያስከብሩ የተላኩ ወታደሮች ዛሬም ድረስ ለአመታት እዛው ከትመው ይገኛሉ። ከችግሮቹ በስተጀርባ ጠንካራና ስውር የውጪ ጣልቃ ገብነት ያለበት በመሆኑ መቼ እንደሚፈታ እንኳን ለመገመት አስቸጋሪ ሆኗል።

በተቃራኒው ህብረቱ አቅሙን አጎልብቶ እየሰራባቸው የሚገኙ ስራዎች መኖራቸው ደግሞ ትልቅ ተስፋ ሰጪ እውነታ ነው። ለዚህ በቅርቡ በሀገራችን ተከስቶ የነበረውን ችግር ለመቅረፍ የተደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤት ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

ከአመት በፊት ነገሮች በተጋጋሉበትና በሀገሪቱ ውጥረት በነገሰበት ወቅት የድርድር ሃሳብም ሆነ የድርድሩ ሂደት በአሜሪካና በአውሮፓውያን መካሄድ አለበት የሚለው እሳቤ የብዙዎችን ቀልብ የሳበ ብቻ ሳይሆን ስኬታማ እንዲሆን ብቸኛ መንገድም ተደርጎ ተወስዶ ነበር።

ከእልህ አስጨራሽ ትንቅንቅ በኋላ ይህን እሳቤ ወደጎን በመተው ወደ አፍሪካ ህብረት የተሄደበት መንገድና የተገኘው ውጤት አፍሪካ የራሷን ችግር በራሷ የመፍታት አቅም እንዳላት በተጨባጭ ያሳየ ነበር። ተሞክሮው በእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ለሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ተስፋ ሰጭ እንደሚሆን ይታመናል ።

በርግጥ አፍሪካውያን የውጪ ጣልቃ ገብነትን አሸንፈው በራሳቸው ፈቃድ ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያደርጓቸው ጥረቶች በብዙ ተግዳሮቶች የሚፈተኑ ናቸው፡፡ ይህንን ፈተና አሸንፈው ለመሻገር አንድነታቸውን በማጠናከር፣ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማሳደግ፣ በዚህም በአለም አቀፍ ደረጃ ድምጻቸው እንዲሰማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ደግሞ የህብረቱ አስተዋጽኦ ከፍያለ እንደሚሆን ይታመናል።

የአህጉሪቱ ሀገራት ጠንካራ ኢኮኖሚ ገንብቶ ቢያንስ በምግብ እህል ራሳቸውን መቻል እራሳቸውን ሆነው ለመገኘት ወሳኝ ነው። ያላቸውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፤ ሊሰራ የሚችል የወጣት ጉልበት በማቀናጀት ሊንቀሳቀሱና ከተያዙበት የድህነት ወጥመድ ሊወጡ ይገባል። ይህም በመካከላቸው ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ትርጉም በሚኖረው መንገድ በማሳደግ የጋራ ተጠቃሚነትን መፍጠር ይቻላል።

ይህ እውነታ ዛሬም በድንበር ከተሞች አካባቢ ብቻ ተወስኖ የሚገኘውን የአፍሪካ ሀገራት በየንግዱ ግንኙነት በማሳደግ ጠንካራ የንግድ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ነው። ለዚህ ደግሞ ሀገራትን በሚያስተሳስሩ መሰረተ ልማቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ወሳኝ ነው። ህብረቱ በዚህ ረገድ ምን ያህል ሊጓዝ እንደሚገባ ማሰቡ አይከብድም።

የአፍሪካ ሀገራት መንግስታትና ህዝቦች ዐይንና ጆሮ / የቅርብ ሩቅ አድርጎ ያስቀመጣቸው በየሀገራቱ መካከል ያለው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የላላና የየሀገራቱ መንግስታት ድጋፍ የሌለበት መሆኑ ነው። በመሰረቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የአፍሪካ ሀገራት የድንበር ወሰን ሀገራቱን ለግጭት የሚዳርግ አውሮፓውያን በቅኝ ግዛት ዘመን የተሰራ አርቴፊሻል አከላለል ነው።

ይህ አርቴፊሻል የድንበር ወሰን አከላል ወደነበረበት ይመለስ ለማለት ሳይሆን የአፍሪካ ሀገራት በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ተቀራርበው ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር መልካም መደላድልን መፍጠር ያስችላል ለማለት ያክል ነው።

ህብረቱ በአጎራባች ሀገራት መካከል ያለውን የህዝብ ለህዝብ ትስስር ማጠናከርና በንግድ ማስተሳሰር የሚችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ በአንድ የገንዘብ ኖት መጠቀም ሳያስፈልግ በሀገራቱ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ማጠናከር ይቻላል።

ለምሳሌ የምስራቅ አፍሪካን ሀገራት ብንወስድ በየድንበሮቻቸው አካባቢ የሚገኙ ህዝቦች በአብዛኛው ተመሳሳይ ቋንቋ የሚጠቀሙና ተመሳሳይ ማንነት ያላቸው ናቸው። ይህም በንግድ ልውውጥ ረገድ የምርት ፍላጎትና አቅርቦት ከሞላ ጎደል ተቀራራቢና ተመሳሳይ ስለሚሆን የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያስገኝ ይሆናል።

ህብረቱ ሆነ የአህጉሪቱ መሪዎች የአህጉሪቱን ህዝቦች ወደተሻለ ሕይወት ማሻገር በሚያስችሉ የጋራ አጀንዳዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ደግሞ የጋራ ራእይ ሊኖራቸው ፤ ለራእዩም ስኬት ቁርጠኛ ሊሆኑ ይገባል። ከህብረቱ ጉባኤ የሚጠበቀውም ይኸው ነው።

# “በትግራይ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ሁሉን አሳታፊ ሊሆን ይገባል”

**- አረጋዊ በርሔ (ዶክተር)**
**የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል አዲስ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሁሉንም ያሳተፈ መሆን እንዳለበት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ትዴፓ/ ሊቀ-መንበር አረጋዊ በርሔ (ዶክተር) ተናገሩ፡፡

አረጋዊ በርሔ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲስ የሚዋቀረው ጊዜያዊ የትግራይ አስተዳደር ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና ከኅብረተሰቡ የተውጣጣ ተወካዮች ያካተተ መሆን አለበት።

ጊዜያዊ አስተዳደሩ ሁሉንም በሳተፈ መልኩ ማዋቀር ከተቻለ የትግራይን ሕዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በዘላቂነት የሚቀርፍ ማድረግ ይቻላል ሲሉ ዶክተር አረጋዊ ገልጸዋል።

ጊዜያዊ አስተዳደሩ የሰብዓዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባ ስራ ማከናወን እንዳለበትም ጠቁመው፤ የወደፊት ሃገራዊና ክልላዊ አቅጣጫዎችን እንዲሁም ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባ አመሰራረት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ አዲስ የሚዋቀረው ጊዜያዊ አስተዳደር መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ሕጋዊ የሆኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት እንደሚሆን ተገልጾ ነበር ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ የጊዜያዊ አስተዳደሩ የማዋቀር ሂደቱን በተባለው ልክ ተፈጻሚ ስለመሆኑ ግምገማና ቁጥጥር ሊደረግበት እንደሚገባም አሳስበዋል።

ዶክተር አረጋዊ እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ በትግራይ ክልል የሚገኙ ዜጎች የተጋረጡባቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት በዋናነት የፖለቲካ ባህሉን መቀየር



ያስፈልጋል። በተለይም በጋራ የመስራትን የፖለቲካ ባህል በማዳበር ችግሮችን በተባበረ ስሜት ለመፍታት የሚያስችል ቅንጅት ያስፈልጋል።

በቀጣይ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ጠንካራ፣ ሕጋዊ ማዕቀፍ ያለው፣ ሁሉን አቃፊና የህዝቡን መሰረታዊ ጥያቄ በትክክል የመመለስ አቅም ያለው መሆን አለበት ሲሉ ዶክተር አረጋዊ ተናግረዋል።

የትግራይን ህዝብ ችግር ሊያቃልል የሚችል የሽግግር አስተዳደር እንዲመሰረትና መዋቅራዊ አሰራሩም የተደራጀ እንዲሆን የፌደራሉ መንግስት አፅንዖት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ያሉት የትዴፓ ሊቀመንበር፤ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ሕብረተሰቡ ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ አስተዳደሩ የሚደራጅበት መንገድ ላይ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም አስረድተዋል።

ነገሮች ወደ ነበሩበት ግጭት እንዳይመለሱና የመጣው ሰላም መልሶ እንዳይደፈርስ ሁሉም አካላት የሚያምኑበትና የተስማማበት አደረጃጀት መፈጠር አለበት ብለዋል። መንግስትም ለጊዜያዊ አስተዳደሩ ስራዎች መሳካት አስቀድሞ መስራት ያለበትን ዝግጅት በሕገ መንግስታዊ ግዴታው መሰረት በመወጣት ለሂደቱ መሳካት የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ዶክተር አረጋዊ እንዳስታወቁት፤ ፓርቲዎችም የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት በመወጣት ሂደቱ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ ማገዝ አለባቸው። ትዴፓ የሕዝቡ መሰረታዊ ጥያቄ ቅድሚያ ተሰጥቶት ለመስራት የጊዜያዊ አስተዳደሩ ምስረታ የተሳካ መሆን እንዳለበት እምነት አለው።

ባለፉት ጦርነቶች ምክንያት ሕዝቡ ላይ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በስነ-ልቦና ከፍተኛ ጫና ስለነበረበት አዲስ የሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ችግሮቹን ታሳቢ ያደረገ መፍትሄዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የትግራይ ሰላም ማጣትና አለመረጋጋት ጉዳቱ ለሁሉም እንደተረፈው ሁሉ የትግራይ መረጋጋትና ሰላም መሆን ለመላው ሀገሪቱ ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ ሰላም ፈላጊ የሆነው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በትግራይ ለሚመሰረተው ጊዜያዊ አስተዳደር ሙሉ ድጋፉን ሊሰጥ እንደሚገባ ገልጸዋል።

## “አፍሪካውያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እና በሜካናይዜሽን እንዲያርሱ የሚያስችል ስራ መስራቷንም ጠቅሰዋል።

ለአብነትም በዘንድሮው ዓመት ኢትዮጵያ ስንዴ ለጎረቤት የአፍሪካ ሀገራት ማቅረብ መቻሏን አውስተው፤ በቀጣይም ምርታማነትን በማሻሻል በአፍሪካ ያለውን የምግብ ፍጆታ እጥረት ለመቅረፍ የበኩሏን ለመወጣት እንደምትሰራ አብራርተዋል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ “የሌማት ትሩፋት” የተሰኘና የምግብ ምርቶችን ማስፋት ላይ ትኩረቱን ያደረገ መርሃ ግብር መጀመሯን ተናግረዋል።

መልማት ከሚችለው የአህጉሪቷ መሬት ውስጥ 65 በመቶ የሚሆነው አሁንም ገና ጥቅም ላይ አለመዋሉን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአፍሪካ 75 በመቶ የሚሆኑ ዜጎች በረሀብ ላይ ናቸው፤ በቀጣይ ግብርናን ማዘመን ላይ በትኩረት ልንሰራ ይገባል ብለዋል፡፡

ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘም አፍሪካ ለአየር ንብረት መዛባት አስተዋጽኦዋ አነስተኛ ቢሆንም እየተጎዳች መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ለመቅረፍ አፍሪካውያን መስራት ይገባቸዋልም ብለዋል።

ኢትዮጵያም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ባለፉት አራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞች መትከሏን ጠቅሰው፤ ይህ ተግባር በመላው አፍሪካ እንዲሰፋ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች እየተገበረች መሆኗንም በንግግራቸው ጠቁመው። እንደ ቴሌኮም ያሉ አገልግሎት ሰጪና የፋይናንስ ዘርፎችን ለግሉ ዘርፍ ክፍት በማድረግ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ሀገር በቀል ማሻሻያ መተግበሯን አውስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው የአፍሪካ ህብረት ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት አህጉሪቷን የሚጠቅሙ በርካታ ተግባራት ማከናወኑን ጠቅሰው፤ ነገር ግን አሁንም በርካታ ስራዎች ከፊታችን ይጠብቁናል ነው ያሉት፡፡

አፍሪካ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ሊኖራት ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ ከአንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት አፍሪካ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታውን ምክር ቤት ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በቂ ውክልና የላትም ነው ያሉት፡፡

ከዚህ አኳያ አፍሪካ በጸጥታው ምክር ቤት ቢያንስ አንድ ቋሚ መቀመጫና የተለዋጭ አባላት ቁጥር ካለበት እጥፍ ሊሆን ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን የሚሰጣቸውን የተዛባ ዕይታ ለማስተካከል የራሳቸውን ታሪክ ነጋሪ የመገናኛ ብዙኃን ማቋቋም ይገባቸዋልም ብለዋል፡፡

“ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ በነበረችባቸው ጊዜያት ስንፈልጋችሁ ከጎናችን የነበራችሁ አፍሪካውያንና አጋሮቻችን ላቅ ያለ ምስጋና ይገባችኋል” በማለትም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

36ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ “የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ትግበራ ማፋጠን” በሚል መሪ ሃሳብ አዲስ አበባ ላይ እየተካሄደ ይገኛል።

## ለአፍሪካ ሰላምና ልማት መረጋገጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ህብረቱ የበለጸገች አህጉርን እውን ለማድረግ አበረታች እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ጠቁመው፤ የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብትና ብዝሀ ባህልና ቋንቋ ባለቤት ለሆነው የአፍሪካ ሕዝብ ትልቅ ጥቅም እንዳለው ገልጸዋል::

እንደ ዋና ጸሐፊው ገለጻ፤ ህብረቱ በሥራ ዕድል ፈጠራ ነፃ የንግድ ቀጣና ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ የሰጠው ትኩረት የሚደነቅ ነው:: ይህም ለአፍሪካውያን በተለይም ለወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠርና ብልጽግናን ለማረጋገጥ ያስችላል:: ለዚህም መሪዎች የሚያሳዩትን ቁርጠኝነት አድንቀዋል::

ነጻ የንግድ ቀጣናን ማሳለጥ ለስራ እድል ፈጠራ ወሳኝ ነው ያሉት ጉቴሬዝ፤ አፍሪካ እኤአ በ2063 ለያዘችው አጀንዳ ያላትን ሀብት በመጠቀም ሕዝቡ ያለበትን ችግር ለመፍታት ያግዛል:: ለዚህ ግብ ስኬት ደግሞ አለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት እገዛ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል::

የአፍሪካ ሕዝቦች የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች እረዳለሁ ያሉት ጉተሬዝ፤ የሀብት አጠቃቀም፣ ከኮቪድ ወረርሽኝ መኖር፣ የሩሲያና የዩክሬን ጦርነት መባባስ የኑሮ ውድነት የሚያስከትለው መዘዝ ተባብሷል:: ይህን ለመግታት ሁሉም በጋራ ሊሰራ ያስፈልጋል:: በአፍሪካ ህብረትና በተባበሩት መንግስታት መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ጠንካራ እንዲሆን ይሰራል ብለዋል::

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለአፍሪካ ህብረት አመራርና ለአህጉሪቱ ሰላም፣ደህንነትና ልማት መረጋገጥ ያለውን ቁርጠኝነት የገለጹት ዋና ጸሐፊው፤ የአህጉሪቱ ትልቅ ፈተና የሆነውን ድርቅ ለመግታት ዓለም አቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል:: እንዲሁም አፍሪካ በድህነት ቅነሳና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በምታደርገው ጥረት ድጋፍ እናደርጋለን ብለዋል::

የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የአፍሪካ ሀገራት አበረታች ስራን እየሰሩ ነው ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ትልቅ ሚና አለው:: ይህም ተጠናክሮ መሄድ እንዳለበት አሳስበዋል::

በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአፍሪካ ድርቅ ለተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚውል 250 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል::

## ‹‹ለአፍሪካ ዕድገት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቁርጠኛ ነኝ፡፡›› ይህን ትልቅ ኃላፊነት ከሴኔጋል ስንረከብ በአህጉሪቱ ሰላምና ደህንነት በማስፈን፣ ሽብርተኝነትን በመዋጋት፣ በስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ላይ ውጤታማ ስራን መስራት ያስፈልጋል፡፡

አፍሪካ በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ውስጥ ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት የተጠየቀው ጥያቄ በሂደት ላይ ነው ያሉት ኡስማኒ፤ ይህ ስኬታማ እንዲሆን በትኩረት ይሰራል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት አፍሪካ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የፋይናንስ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አፍሪካ የምትፈልገው ከዚህ ድጋፍ ባሻገር በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት ነው፡፡ ይህን ደግሞ ይቀበሉታል ብዬ አስባለው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን በላይ ሕዝብ መኖሪያ የሆነችው አፍሪካ በተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ምክር ቤት ውስጥ መቀመጫ ሊኖራት ይገባል፡፡ ‹‹ይህ ጥያቄ የፍትሐዊነት ጉዳይ በመሆኑ በቀጣይ መልስ ያገኛል ብዬ አስባሁ›› ለተግባራዊነቱም ተግቼ እሰራለሁ ሲሉ ኡሱማኒ ገልጸዋል፡፡

አፍሪካ ‹‹አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሔ›› በሚለው መርህ ችግሮቿን ያለማንም ጣልቃ ገብነት በራሷ አቅም መፍታት ጀምራለች፡፡ ለዚህ ትልቅ ምሳሌ በኢትዮጵያ በሰሜኑ ክፍል የተፈጠረውን ግጭት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረሰው ስምምነት ሰላም መፈጠሩ ትልቅ ምሳሌ መሆኑን የጠቆሙት ኡስማኒ፤ ሰላምን በአፍሪካ በማስፈን ኢኮኖሚዋ ያደገች፣ ዲሞክራሲ የሰፈነባት፣ የዜጎች ደህንነት የተረጋገጠባት አፍሪካን እውን ለማድረግ በትብብር መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የሴኔጋል ፕሬዚዳንትና ተሰናባቹ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበር ማኪሳል በበኩላቸው፤ በአፍሪካ የማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ቁልፍ አጀንዳ አድርጎ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ለመልማት ትልቅ አቅም አለን፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለማሳደግ በቂ የኃይል አቅርቦትን ማጠናከር፣ የስራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ ይገባል ነው ያሉት፡፡

በአፍሪካ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ቁልፍ ተግባር መሆን አለበት፡፡ የምግብ ዋስትናን ያላረጋገጠ አገር ብልጽግናን መመኘት አይችልም፡፡ ቅድሚያ ሰጥቶ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ሲሉ ማኪሳል ገልጸዋል፡፡

በጉባኤው ላይ ንግግር ያደረጉት የኅብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የዘንድሮ የህብረቱ ጉባኤ ለመገምት አስቸጋሪ እና አስፈሪ በሆነው የዓለም ሁኔታ ውስጥ የሚካሄድ መሆኑ ለየት ያደርገዋል።

ጂኦ ፖለቲካዊ ፉክክሮች እና የተበታተነ የኢኮኖሚ አስተዳደር የአለም መገለጫ የሆነበት ወቅት ላይ እንገኛለን ያሉት ሙሳ ፋኪ፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት የዓለም የኢኮኖሚ እድገት ከዚህ በፊት በነበረው ፍጥነት እየሄደ አይደለም። የዋጋ ንረት በአለም ታይቶ በማይታወቅበት መጠን ጨምሯል። የሀገራት የእዳ ጫና እና የኢነርጂ ቀውስ ምርትን ለማምረት የሚወጣው ወጪ ከፍ እንዲል አድርጎታል።

በዓለም ላይ ያለው ሁኔታ በአህጉሪቱ ላይ ጫና የሚያሳድር ነው ያሉት የህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር፤ እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም የአፍሪካ ሀገራት በጋራ መቆም አለባቸው ብለዋል፡፡ የህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር እንደተናገሩት፤ አህጉሪቱ በዓለም ላይ ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ መቋቋሚያ ዘዴዎችንም መቀየስ አለባት። በአፍሪካውያን መካከል ያለው ወንድማማችነት እና ትብብር ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊጠናከር ይገባል። የአፍሪካ የፋይናንስ ተቋማትን ማቋቋምና ማጠናከር ልዩ ትኩረት ይሻል።

ወቅቱ አፍሪካዊያን የነጻ ገበያ ቀጣና ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው ያሉት ሙሳ ፋኪ፤ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነትን መሬት ላይ ለማውረድ መሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ዲጂታላይዜሽን ላይ ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ብለዋል።

ያለ መሰረተ ልማት እና ዲጂታላይዜሽን ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነቱን እውን ለማድረግ አዳጋች መሆኑን በመገንዘብ የአፍሪካ መሪዎች ለእነዚህ ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## “ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ፤”

36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች መደበኛ ጉባዔ “የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራን ማፋጠን” በሚል መሪ ሃሳብ እየተካሄደ ሲሆን 42ኛው የአፍሪካ ህብረት የስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ስብሰባ ባለፈው እሮብና ሀሙስ በሕብረቱ ዋና መቀመጫ አዲስ አበባ ተካሂዷል። ምክር ቤቱ ለሁለት ቀናት ባደረገው ስብሰባ የሕብረቱ አባል ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና ተወካዮች ተሳትፈዋል። ከዋናው ጉባኤ ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች ጋር ጠቃሚ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል። በአንድ በኩል ወዳጅንና አጋርን የማብዛት ፤ በተለያየ ምክንያት የተያዘን ብዥታ የማጥራት ስራ እየተሰራ መሆኑ ተመልክቷል። ስለ ታላቁ የሕዳሴ ግድብና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ስለነበረው ጦርነትና የሰላም ሒደት ገለጻና ማብራሪያ ከሚሰጥባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ ይገኙበታል።

ከ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ ሕዝብ ላላት አህጉር ነጻ የንግድ ቀጣና እስትንፋሷ ነው ። አብዛኛው ወጣት ለሆነው ዜጋዋ የስራ ዕድል ይፈጥራል። ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ይበረታታል፤ በሀገራቱ መካከል የእርስ በርስ ንግድን ያሳልጣል። ሰፊ ገበያና የገበያ ትስስር ይኀለብታል። ለአፍሪካዊ ሸማች ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርባል። ሸማቹ በጥራትና በዋጋ አወዳድሮ የመግዛት እድል ይኖረዋል። ሀገራቱም ሆነ አህጉሯ ፈጣንና ተከታታይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማስመዝገብና ርቆ የተሰቀለውን ብልጽግና ለማቅረብ ነፃ የንግድ ቀጣና ትስስሩ የማይተካ ሚና አለው።

በርካታ ሀገራት ላለፉት 17 ዓመታት ሲታሸና ሲኀሸ ባጅቶ ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ ወደ ሙከራ ትግበራ ገብቷል። ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነቱን ከማጽደቅ አልፈው በነጻ የንግድ ቀጣናው የሚካተቱ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለይተው አቅርበዋል። ሀገራችንም ለኢትዮጵያና ለቀጣናው የገቢና ወጪ ንግድ መቀልጠፍ ትልቅ ሚና ያለውን በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ባለፈው ዓመት በይፋ ስራ ማስጀመሯ ይታወሳል። በነጻ የንግድ ቀጣናው የሚካተቱ ምርቶችንና አገልግሎቶችን መለየቷ እየተነገረ ቢሆንም እንደሌሎች ሀገራት የሸማቹን ጥቅም ከግንዛቤ ያስገባ ይሁን አይሁን ወደፊት የምናየው ይሆናል።

የሆነው ሆኖ ነጻ የንግድ ቀጣናው ስትራቴጂካል ግብ በመጀመሪያ ኢኮኖሚያዊ እድገትና አንድነት በማስከተል ደግሞ ፖለቲካዊ አንድነት በማምጣት የፓን አፍሪካኒዝምን ህልም እውን ማድረግ ነውና ይበል የሚያሰኝ ነው። ሆኖም ከዚያ በፊት ግጭትን ከአህጉሪቱ ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት ይበልጥ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚሉ ወገኖች አሉ ። ከ3 ነጥብ 4 ትሪሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ጥቅል አህጉር ውስጥ ምርት /GDP/ እና ከኤርትራ በስተቀር 55 ሀገራትን በነጻ የንግድ ቀጣናዊ ትስስር የማካተት ነገር አልጋ በአልጋ እንደማይሆን ቢታመንም ጉዞው መጀመሩ በራሱ በልክ እውቅና ሊቸረው ይገባል።

ዛሬ ቻይና በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎቿን ከድህነት አረንቋ ማውጣት እና በዓለማችን ሁለተኛውን ግዙፍ ኢኮኖሚ መገንባት የቻለችው በሯን ለንግድ በመክፈቷ ነውና አፍሪካም የዘገየ ቢሆንም ይህን ዳና ለመከተል መወሰኗ ይበል የሚያሰኝ ነው። በጸረ ቅኝ ግዛት ትግልና በፓን አፍሪካኒዝም መካከል ሲመናተል የኖረውን አህጉራዊ ተቋም ታሪካዊ ዳራ በአለፍ ጠቀም እንቃኝ። “የአፍሪካ ህብረት ራሳቸውን “ ንጉሠ ነገሥት “ ብለው በሚጠሩት የቀድሞው የሊቢያ ገዥ ኮሎኔል ሙአመር አል ጋዳፊ ሃሳብ አመንጭነት እ .አ .አ መስከረም 9 ቀን 1999 በትውልድ ቀያቸው ሲርጥ ከተማ በተደረሰ ስምምነት መሰረት 55 አባል ሀገራትን በማካተት እ .አ .አ ግንቦት 26 ቀን 2001 አዲስ አበባ ላይ የተቋቋመ አህጉር አቀፍ ህብረት ነው።

ህብረቱ እ. አ .አ በግንቦት 25 ቀን 1963 በ32 መስራች ሀገራት በአዲስ አበባ ተቋቁሞ የነበረውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን /አአድ/ ተክቷል ። ድርጅቱ ከተቋቋመለት ዓላማ ቀዳሚ የሆነውን ከ1 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ የአህጉሩን ዜጎች መብትና ነፃነት እንዲከበር ከመስራት ይልቅ የአምባገነን መሪዎች ጠበቃና መከታ በመሆኑ ተቺዎቹ “ የፈላጭ ቆራጮች ክበብ “ (Dictators’Club) ሲሉ ይሳለቁበት ነበር ። አሁን አሁን ግን መፈንቅለ መንግሥትን ከማውገዝ አልፎ ከአባልነት እያገደ፣ ማዕቀብ እየጣለ እና በመፈንቅለ መንግሥት ወደ አገዛዝ የመጡትን ምርጫ በአጭር ጊዜ እንዲያካሂዱ ከማስገደድ ጀምሮ በኃይል ለማውረድ እስከማስፈራራት ደርሷል። የወተት ቢሆንም ጥርስ እያበቀለ ይመስላል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እንርሳውና የኮሎኔል ጋዳፊ የጡት ልጅ እንደሆነ የሚነገርለት የአፍሪካ ህብረት ሌላው ይቅርና አባት ሀገር ሊቢያ አፍንጫው ስር በቁሙ እንደ የአሸዋ ላይ ሰቀላ ሲፈራርስ አይቶ እንዳላየ አለፈ እንዳይባል ፤ አምባገነኑንና ለረጅም ዓመታት አገዛዝ ላይ ያረጀውን የማእከላዊ አፍሪካ ፕሬዚዳንትን እና የአፍሪካ ህብረት የወቅቱ ሊቀ መንበር የነበረውን ቴዎድሮ ኦቢያን ንጉየማ ቀውሱን እንዲፈታና በሊቢያ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እንዲያመጣ መላኩ ለአፍሪካ ፣ ለምዕራባውያንና ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ስላቅና ልግጫ ነበር ። ህብረቱ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ አግባብ አንድም ግጭት ፈቶ አያውቅም እየተባለ ሲተች ኑሮ የኢትዮጵያንና የትህነግን ጦርነት ለዛውም በሀገራችን ጥያቄ “ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ” በሚል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ዕርቅ ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱ ይበል የሚያሰኝ ነው።

የሌለን ሰላም ለማስከበር ወደ ዳርፉር ፣ ብሩንዲ ፣ ሶማሊያና ማሊ ሰላም አስከባሪ ኃይል ቢላክም ዛሬ ድረስ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን አልቻለም ። በየመን ፣ በሊቢያ፣ ደቡብ ሱዳንና በካሜሩን የእርስ በእርስ ግጭቶች ማስቆም ስለተሳነው የውክልና ግጭት መናኸሪያ እንደሆኑ ቀጥለዋል። ከአልጀርሱ ስምምነት በኋላ ህብረቱ ላለፉት 20 ዓመታት ዞር ብሎ አይቶት የማያውቀውን የኢትዮ- ኤርትራ ፍጥጫ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ተነሳሽነቱን በመውሰድ እርቅ ማውረድ ችለዋል። ውጥረቱን አርግበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚህ ሳይታበዩ የሱዳን ተፎካካሪ ኃይሎችን እና ወታደራዊ ጁንታውን አቀራርቦ በማደራደር የሽግግር ሥልጣን እንዲጋሩ እና ሰላም በማስፈን የማይተካ ሚና ከመጫወታቸው ባሻገር በሱማሊያና ኬንያ ፣ በኤርትራና በጅቡቲ እና በሌሎች ሀገራት መካከልም ሰላም እንዲወርድ ጥረት አድርገዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግል ተነሳሽነትም ሆነ እንደ ኢጋድ ግጭቶችን በውይይት ፣ በድርድር መፍታት እንደሚቻል በአጭር ጊዜ የሄዱበትን እርቀት ስንመለከት ህብረቱ የሚጠበቅበትን ያህል አለመስራቱን ያሳጣል።

በመጪው ግንቦት ስድስት አስርት ዓመታትን ሊደፍን በጣት የሚቆጠሩ ወራት የቀሩት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት / አ አ ድ/ ወይም የዛሬው የአፍሪካ ህብረትን / 14 ዓላማዎች ቢኖሩትም የጋዜጣው አምድ ስለማይበቃ ዋና ዋናዎቹን ከእነ አፈፃፀማቸው እንመልከት :-

1ኛ . በሀገራትና በሕዝቦች መካከል የበለጠ መቀራረብ፣ ወንድማማችነትና አንድነት መፍጠር ፤ ይህን ዓላማ ከአውሮፓ ሕብረት እንዳለ የተገለበጠና ከወረቀት አልፎ እውን ሊሆን ሊተገበር የማይችል ሲሉ ልሒቃን ያጣጥሉታል። 55 ሀገራትንና ከ2ሺህ በላይ ጎሳዎችን ይዞ ወደ ወንድማማችነት በመጨረሻም የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ አንድነት ፈጥሮ የተባበሩት የአፍሪካ ህብረት United States of Africa / USA/ እውን የማድረግ ጉዳይ ፍጹም የሚታሰብ አይደለም በማለት የሚሞግቱ አሉ። ጋናዊው ጆርጅ አይቴ ከእነዚህ ልሒቃን አንዱ ነው።

የውጭ ግንኙነትና ዓለምአቀፍ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ በመሞገትና በመተንን በሚታወቀው ፎሪን ፖሊሲ መፅሔት “ Disband the African Union “ በሚል ርዕስ ሞጋች ሳይሆን ቀጭን ትዕዛዝ ባስተላለፈ ጹሑፉ ፤ “ ህብረቱ ጠንካራ የሆነውን ማዕከላዊነት ማላላት በአንጻሩ ደካማ አደረጃጀቱን ማጠናከር አለበት። አባል ለመሆን ግልፅና ጠንካራ መስፈርት ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በሀገራቱ መካከል የሚኖረው ግንኙነትም በግልፅ የጋራ ራዕይ ላይ የተመሰረተና በኮንፌደሬሽን የሚመራ መሆን አለበት።

“ የህብረቱ ሪፎርም ፣ በ2020 ተኩስ የማይሰማባት አፍሪካ፣ አዲስ አጋርነት ለአፍሪካ ልማት /ኔፓድ / እ አ አ 2001 ላይ ይፋ ቢሆንም የበላው ጅብ ዛሬ ድረስ አልጮኸም። ጆርጅ ህብረቱ የራሱን ቢሮ መገንባት አለመቻሉ የውድቀቱ ማሳያ ነው ሲል ይሞግታል። አይደለም የህብረቱ አባል ሀገራት 9 ቢሊዮን ዶላር በሙስና አካብተዋል የሚባሉት የቀድሞው የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኦማር አልበሽር ወይም የአንጎላው ፕሬዚዳንት ሴት ልጅና 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር እንደመዘበረች የሚነገርላት ኢዛቤል ዶስ ሳንቶስ በግላቸው ሊገነቡት ይችል ነበር ሲል ይሳለቃል።

2ኛ . ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ፣ መርህንና መልካም አስተዳደር ማበረታታት ፤ ከፍ ብዬ ለመጥቀስ እንደሞከርሁት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዴሞክራሲያዊ ግንባታ ሒደት ጅምር እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ቢሆንም ቀደም ባሉ በርካታ ዓመታት ግን ህብረቱ በአሁጉሩ “ ነፃ ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ “ ያላለው ምርጫ የለም ማለት ይቻላል። ለዚህ ነው ተቺዎቹ የቀረበለትን የምርጫ ውጤት ሁሉ ወዲያውኑ ሳይመረምር ስለሚያረጋግጥ” ራበር ስታምፕ “ ሲሉ ቅፅል የሰጡት። ጆርጅ ከፍ ብዬ በጠቀስሁት መጣጥፉ ፤ “ … ህብረቱ ሌላው ይቅርና ዛሬ ድረስ በዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ ትርጉም ላይ እንኳ መግባባት አልቻለም ።… “ ይላል ።

3ኛ . በአህጉሩ ሰላምን ፣ ደህንነትንና መረጋጋትን ማስፈን፤ ይህ የህብረቱ ዓላማ አይደለም ሊሳካ ተባብሷል።” በ2020 የተኩስ ድምፅ የማይሰማበት አህጉር “ እውን ለማድረግ ከ10 ዓመት በፊት የጣለው ግብ ከሽፏል። ግቡ ሲጣል ግጭት የነበረባቸው ሀገራት ቁጥር ከ10 ያልበለጡ ነበሩ። ዛሬ ላይ ግጭት ውስጥ ያሉ ሀገራት ቁጥር ከ20 በላይ ደርሷል። እነ ሊቢያን ፣ ሶማሊያን፣ የመንን ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንን ፣ ማሊን ፣ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፣ ቡርኪናፋሶን ፣ ማእከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክን፣ ቻድን ፣ ካሜሩንንና ሰሜን ናይጀሪያን በአብነት ማንሳት ይቻላል።

4ኛ . የሰብዓዊና የሕዝቦችን መብቶች በቻርተሩ መሰረት ማስከበር ፤ ህብረቱ የዜጎች ፣ የሕዝቦች ሰብዓዊ መብት በአምባገነኖች ሲጨፈለቅ ፣ ሲጣስ ጥብቅና ይቆም የነበረው ለአምባገነኖች ነው። ኦማር አልበሽር በተለይ በዳርፉር በጦራቸውና ጃንጃ ዊይድ በተባለ ሚሊሺያ ዘግናኝ ግፍ ሲፈፀም ትንፍሽ አለማለቱ ሲያሳዝነን ዓለምአቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርትባቸው ተላልፈው እንዳይሰጡ ሽንጡን ገትሮ ከመከራከር አልፎ ፤ ሀገራት ከዓለማአቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት እንዲወጡ ግፊት ሲያደርግ ነበር ።

5ኛ . በአህጉሩ ምርምርን በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ማበረታታት ፤ የአህጉሩ መለያ የሆኑትን ድርቅና ርሀብ ፣ የእርስ በርስ ግጭትና መፈናቀል ፣ የገነገነ ዘረፋ፣ …፤ ለመከላከል ፤ ምርታማነትን ለማሳደግ ፣ አህጉሩ የሚታወቅባቸውን እንደ ኤች አይ ቪ / ኤድስ ያሉ ወረርሽኞችን ለመከላከል፣ የቴሌኮም ኢንዱስትሪውን እና ዲጂታል ኢኮኖሚውን ለማሻሻል በአጠቃላይ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂውን ለማበልፀግ ምን ሰራ !?

እንደመውጫ በዓለማችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ እንጉዳይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የመጣው ሕዝበኝነት populism ፣ ቀኝ ዘመምነትና አክራሪነት አህጉር አቀፍ እና ድንበር ዘለል ትብብሮችን እያዳከመ ነው ። ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከ70 ዓመታት በላይ ሰላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ የማይተካ ሚና የነበራቸው እነ አውሮፓ ህብረትና የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን / ኔቶ /ችላ እየተባሉ ነው ።

በተለይ “ አሜሪካ ትቅደም ! “ የሚል ሕዝበኛ መፈክር አንግበው ወደሥልጣን የመጡት ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በተባበሩት መንግሥታት ፣ በአውሮፓ ሕብረት፣ በኔቶ እና በሌሎች መሰል ስብስቦች ላይ የተከተሉት የተንሸዋረረ አመለካከት ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮ ነበር ። ፕሬዚዳንት ባይደን “አሜሪካ ተመልሳለች !”ብለው ባያስተካክሉት ኖሮ አደጋ ላይ ወድቀው ነበር።

የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂው ዓለምን ወደ ትንሽ መንደርነት እየቀየረ ባለበት በዚህ ወቅት አክራሪ ብሔርተኞችና ሕዝበኞች ደግሞ መለየትን ፣ መነጠልን እየለፈፉ ዓለምን ግራ እያጋቡ ይገኛል። እንግሊዝ በእነ ትራምፕ አይዞሽ ባይነት ከሕብረቱ መነጠሏ እና በፈረንሳይ፣ በጣሊያንና በምስራቅ አውሮፓ አክራሪ ብሔርተኝነት እየተጠናከረ መምጣቱ ሌላ ስጋት ሆኖ ብቅ ብሏል። ወደ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ሆነ እሱን ወደ ተካው የአፍሪካ ሕብረት ስንመጣ ከውጫዊ ፈተናዎቹ ይልቅ ውስጣዊ ችግሮቹ የከፉ ሆነው እናገኛቸዋለን። አራምደዋለሁ የሚለው በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት አቋም ለችግሩ አንዱ መግፍኤ ነው። የሕብረቱ አባል ለመሆን ምንም አይነት መስፈርት አለመኖሩ ችግሩን ይበልጥ ያወሳስበዋል ። ይሁንና “የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራን ማፋጠን” የሚለው መርሁ ተግባራዊ ከሆነ ዘመኑንም ሆነ ትውልዱን የዋጀ ይሆናል። ከፍ ብዬ ለመጥቀስ እንደሞከርሁት ከአህጉሩ ከ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ከሚበልጠው ሕዝብ ውስጥ አብላጫው ወጣት ስለሆነ የዚህ ታላቅ ራእይ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

የትምህርትና ሥልጠና ፣ የብድር አገልግሎትና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ግንባታ ማኅልበት ወጣቱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ ስለሚያደርግ ልዩ ትኩረት ይሻል ። ለወጣቱ ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ አለመንቀሳቀሱ ፤ ወጣቱን ወደ አመራርነት የሚያመጡ ስራዎችን አለማከናወኑ ፤ የወጣቱ መሰረታዊ ጥያቄ እየሆኑ የመጡት የዴሞክራሲና የነጻነት ጥያቄዎች ላይ እግሩን የሚጎትት መሆኑ በነቃፊዎቹ ዘንድ ዘመኑንም ሆነ ትውልዱን የማይዋጅ ስብስብ በሚል ሲወቀስ ኖሯል። አሁን ግን ይህን ታሪክ የሚቀይር ጅምር እንቅስቃሴ እየተስተዋለ በመሆኑ ተስፋ ተሰንቋል።

አፍሪካንና አፍሪካውያንን ፈጣሪ አብዝቶ ይባርክ!

ሻሎም !

አሜን ።

አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ከአባት የተወረሰው የሕዝብ እንደራሴነት

እፀገነት አክሊሉ

ትደነቅ ጉልዱ ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ ነው። አዲስ አበባ የመወለዷ ትልቁ ምክንያት ደግሞ አባቷ በአሁኑ አጠራር በደቡብ ምዕራብ ክልል ሱሪ ወረዳን በመወከል የሕዝብ ተወካይ ሆነው አዲስ አበባ መምጣታቸው ነው። ትደነቅ ግን እንደ አለመታደል ሆኖ ከአባቷ ጋር ለመኖር አልቻለችም። ምክያቱም ገና የሦስት ዓመት ህጻን ልጅ እያለች ነው አባቷን በሞት የተነጠቀችው፡፡

"...አባቴ የሱሪ ሕዝብ በሰጠው ውክልና ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ ቤተሰቡን ይዞ መኖር ጀምሮ ነበር።በዚህ መካከል ደግሞ እኔ ተወለድኩ።ነገር ግን እኔ ተወልጄ የሶስት ዓመት ልጅ እንኳን ሳልሆን አባቴ ሞተብኝ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለእናቴና ለሌሎች የቤተሰቡ አባላት ከባድ ደንጋጤና ኀዘን የፈጠረ ነበር። በዚህም አዲስ አበባ የሚያስቆይ አቅምም ሆነ ምክንያት ስላልነበረን በቀጥታ ወደ ትውልድ አካባቢ ከእናቴ ጋር ሄድን " በማለት ሁኔታውን ታስታውሳለች፡፡

ከእሷ ጋር አራት ልጆች የነበራቸው እናቷ ልጆቻቸውን በሚችሉት አቅም ሁሉ ለማሳደግ ቢጣጣሩም ኑሮ ግን እንደቀድሞው ሊሆንላቸው አልቻለም።ታላቅ ወንድማቸውንም የአባቷ ጓደኛ ‹‹እኔ አሳድገዋለሁ›› በማለት ወሰዱት።ይህ ለእናቷ ከባድ ቢሆንም አማራጭ ስላልነበራቸው ልጁም የተሻለ ትምህርት አግኝቶ እንዲያድግ ተስማምተው ሰጡት።ስለዚህም እሷና ሁለት ታናናሽ ወንድሞቿ ናቸው ከእናታቸው ጋር የቀሩት።ይህ መሆኑ ደግሞ እነ ትደነቅን ብዙ እድለኛ አላደረጋቸውም።ምክንያቱም የኑሮ ውጣ ውረድ ሲደመር ህመም ሞታቸውን አፋጠነውና የሚወዷቸውንና የሚሳሱላቸውን ልጆቻቸውን ትተው እናቷ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።ከሰባት ዓመት በላይ ከእነርሱ ጋር ሳይቆዩም ሞት ነጠቃቸው።

"...ታላቅ ወንድማችን የአባታችን ጓደኛ ጋር ለማደግ አዲስ አበባ ሲቀር እኔና ሁለት ወንድሞቼ ከእናታችን ጋር ለመኖር ሱሪ ሄድን ፤ እናታችን እኛን ለማኖርና ለማሳደግ በርካታ ሙከራዎች አድርጋለች።ያልሞከረችው የሥራ አይነትም አልነበረም።ሁሉም ሊሳኩላት ግን አልቻሉም፤ በመጨረሻ እሷም እራሷ ታማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች" በማለት የገጠማቸውን አሳዛኝ አጋጣሚ ትናገራለች፡፡

አባቷ ከሞቱ ከሰባት ዓመት በኋላ የአስር ዓመት ታዳጊ እያለች እናቷንም ዳግም ማጣቷ በህጻንነት አቅሟ መቋቋሙ ከብዷት ነበር።ነገር ግን የሕይወትን ውጣ ውረድ ለማሸነፍ ወደፊት እንጂ ወደኋላ ማየት እንደሌለባት ታውቃለች።ነገሩ ዱብዳ ቢሆንባትም ከኑሮ ጋር መጋፈጥን መርጣለች።መኖር ግድ ነውና አማራጮችን እንድታይም ሆናለች።ይህ እድል ትደነቅን ከክርስትና እናቷ ጋር የቀላቀላት ሲሆን፤ በዚያ መኖርና መማር ጀመረች።ከክርስትና እናቷ ልጆች ጋር እንድታድግ ሆነች።

"...በወቅቱ እኔ ከክርስትና እናቴ ጋር ብኖርም ሁለቱ ወንድሞቼ ደግሞ ወደገጠር ነበር የተላኩት።ገጠር ደግሞ ለመማርም ለመኖርም አይመችም።በዚህም እኔም አዝን ነበር። ወንድሞቼን አላያቸውም፤ ደህና ይሁን አይሁኑ አላውቅም። እናም ሁሉ ነገር ከብዶኝ እኖራለሁ።ይባስ ብሎ ደግሞ ብዙም ሳልቆይ እኔም ራሴ ህጻናት ማሳደጊያ እንድገባ ሆንኩ" ትላለች ቤተሰባቸውን ካጡ በኋላ ያለው የልጅነት ጉዟቸው ምን እንደሚመስል ስታወሳ፡፡

ሐዋሳ ‹‹ትኩረት ለህጻናትና ለሴቶች›› የሚባል ድርጅት ውስጥ ገብታ ትምህርት የጀመረችው ትደነቅ፤ እዚህም ሆና የወንድሞቿ ጉዳይ እንቅልፍ ይነሳት ነበር፤ በጣምም ያሳዝናታል።በስልክ እንኳን ድምጻቸውን መስማት የምትችልበት አጋጣሚ አልነበረም።እናም ሁኔታው እጅግ በጣም ከበዳት።ይህ ደግሞ በጤናዋ ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን አስከትሎባታል።

"...በእናቴ ኀዘን፣ በወንድሞቼ ናፍቆት ምክንያት ከፍ ያለ ጭንቀት ውስጥ ገባሁ።በዚህ ደግሞ ለወራት ያህል ሆስፒታል መተኛት ነበረብኝና ተኛሁ።በዚያም ምንድነው የሚያስጨንቅሽ ? ለምንድን ነው የምትረበሺው? በማለት የህክምና ባለሙያዎቹ እንዲሁም የማሳደጊያው ሰዎች ሲጠይቁኝ መልሴ ወንድሞች እንዳሉኝ እነሱን ማግኘት እንደምፈልግና ጤንነታቸው እንደሚያሳስበኝ ነገርኳቸው" በማለት የተፈጠረውን ሁኔታ ትናገራለች፡፡

ትደነቅ ከወራት ህመም በኋላ ከሆስፒታል ወጥታ ወንድሞቿን እንድታገኝ ተደረገች ፤ እሷ በምትኖርበት እርዳታ ድርጅት ውስጥ እነሱም እንዲኖሩ ተፈቀደላት።ይህ ደግሞ ለትደነቅ ብዙ ነገሮችን ሰጥቷታል።ራሷን እንድታዳምጥ፣ ሙሉነት እንዲሰማትና እንድትረጋጋ አድርጓታል።የእናትና አባቷ ኀዘን በቀላሉ የሚረሳ ባይሆንም መጠነኛ መረጋጋት ውስጥ እንድትገባ አስችሏታል።

"...ወንድሞቼ እኔ ያለሁበት ተቋም ውስጥ ሲመጡ ከፍተኛ የሆነ መረጋጋት ተሰማኝ፤ ወደ ጤንነቴም በመመለሴ ትምህርቴን በትኩረት ለመማር ወሰንኩ " በማለት በእናትና አባቷ ሞት እንዲሁም ከወንድሞቿ መለየቷ አድርሶባት የነበረውን ሥነ ልቦናዊ ጫና የምታስታውሰው ትደነቅ፤ ቤተሰብ ማጣት ምን ያህል ከባድ የሥነ ልቦናዊ ጫና ውስጥ እንደሚከት ነገር ግን መልካም ነገሮች ሲመጡ መረጋጋት እንደሚቻል ታወሳለች።በተለይም የምንጨነቅላቸው ሰዎች ከጎናችን ሲሆኑ በብዙ ነገሮች ራሳችንን ማጠንከር እንደምንችልም ታስረዳለች።ምክንያቱም እርሷ ወንድሞቿን በማግኘቷ ትልቅ ጥንካሬን አግኝታለች።ከሌሎቹ ልጆች ጋርም ጥሩ ግንኙነትን አዳብራለች።የእህት፣ የወንድም፣ የቤተሰባዊነት ቅርርብንም በሚገባ እየተረዳችው መጥታለች። ይህ ደግሞ በእጅጉ ደስተኛ አድርጓታል ፤ደስተኛ መሆኗ ደግሞ በትምህርቷ ላይም ውጤቱ ይታይ ነበር።

### ኑሮ በህጻናት ማሳደጊያ

ማሳደጊያ ከብዙ ቦታ ብዙ ዓይነት ህጻናት የሚመጡበት፤ የማይተዋወቁ ልጆች ቤተሰብ ሆነው የሚኖሩበት ቤት ነው።ሁሉም ሰው ቤተሰቡ አጠገቡ ኖሮ ቢቆጣጠረው፣ መንገድ ቢመራው፣ በሚቸግረው ነገር ላይ ድጋፉን ቢያሳየው ደስ ይለዋል።ይህ አልሆን ሲል ግን ፈጣሪ እድሉን በሰጣቸው መልካም ሰዎች በአቋቋሙት ማሳደጊያ ውስጥ ማደግ ግድ ይሆናል። ምክንያም ልጆች የትም ሜዳ ከሚቀሩ የተሻለ አማራጭ ነው። እነ ትደነቅም ቤተሰብ ባይኖራቸውም አንድ ላይ ሰብስቦ የሚያሳድግ ማሳደጊያ ማግኘታቸው ከብዙ ነገር ጠብቋቸዋል፤ ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩም አድርጓቸዋል።ኑሮ ብዙም አልከፋቸውም፡፡

ማሳደጊያው ልጆቹን ያስተምር የነበረው የግል ትምህርት ቤት በመሆኑ እነ ትደነቅም እዛው የግል ትምህርት ቤት እንዲገቡ ሆነ።ትደነቅ ግን ቀድሞ ከለመደችው የትምህርት አሰጣጥ የተለየ ሆኖባት ግራ መጋባቷ አልቀረም። ይህም በጣም ከብዷት ነበር።ሆኖም ልጅነቷ አግዟት አካባቢውን እንዲሁም የትምህርት አሰጣጡን በቶሎ ለመላመድ ችላለች፡፡

"...በማሳደጊያ ቤት ጅማሬዬ በጣም ብዙ የሚከብዱ ነገሮች ቢገጥሙኝም ብዙ ነገሮችን በዚያው ልክ ተምሬበታለሁ።ከዚህም ብወጣ ቤተሰብ የለኝም የሚለውንም ያሳየኝ ነው። ስለዚህ ጠንካራ ሆኜ ማለፍ አለብኝ በማለት በቀጥታ ራሴን ወደማጠንከር እንድገባ ሆኛለሁ። በዚህም ተሳክቶልኛል ብዬ አስባለሁ" ትላለች፡፡

ትደነቅ የ12ኛ ክፍል ተማሪ እያለች የማታውቀው አጋጣሚ ገጥሟት ነበር።ይህም የነበሩበት የማሳደጊያ ድርጅት ይዘጋል የሚል ዜና ወደጆሮዋ መምጣቱ ነው።እንዲህ መሆኑ ቢያሳዝናትም በእሷ አቅም የሚሆን ነገር የለምና የመጣውን ለመቀበል ወሰነች።በቀጣይ ደግሞ የት ነው የምንሄደው፤ ማን ጋር ነው የምንጠለለው የሚለው የማይመለስ ጥያቄ ሆነባት ታናናሽ ወንድሞቿ የእሷ ሃላፊነት ናቸውና ምን ላድርግ የሚለውን በታዳጊነት አዕምሮዋ አወጣች አወረደች።ለጊዜው የመጣላት መፍትሔም ወደ ፈጣሪዋ መጸለይ ብቻ ነበር።ጸሎቷም ተሰምቶ እሷንም ወንድሞቿንም ፈጣሪ ጥሎ አልጣላቸውም።ወዲያውኑ ‹‹አቤኔዘር ዴቨሎፕመንት ሰፖርቲንግ አሶሴሽን›› የሚባል የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት ሊቀበላቸው እንደ ወላጅ ቤተሰብም ሆኖ ሊያሳድጋቸው ተስማማ።ደስተኛ የሚያደርጋትን ነገር አገኘችበትም።እንደውም ስለዚህ ማሳደጊያ ድርጅት ስታስረዳ እንዲህ ነበር ያለችው ‹‹ሁለተኛው ማረፊያችን እንደ ማሳደጊያ ድርጅት አይደለም፤ ይልቁንም እንደ ቤተሰብ ነበር ፤ ብዙ የልጅነት፣ የወጣትነት ትዝታም እንዲኖረኝ አድርጓል።በፊት የነበርንበት ማን አለ፤ የለም የሚለው በምዝገባ ነበር የሚታወቀው፤ ይሄኛው ደግሞ በአካል ተገናኝተን ልክ እንደ አባትና ልጅ ተቀራርበን ነው ለአንድ ዓመት ያህል የቆየሁት"

### ሚንጊ (ገፊ)

በሐመር ብሄረሰብ ላም፣ በግ ወዘተ ... ጥርስ ማብቀል የሚጀምሩት በታችኛው ድዳቸው ስለሆነ ቅዱስ ይባላሉ። አህያ ፈረስ፣ ጅብ በላይኛው ድዳቸው ስለሚያበቅሉ ርኩስ ይባላሉ። የሰው ልጅም የወተት ጥርሱን በታችኛው ማብቀል ሲገባው እንደ እርኩሳኑ በላይኛው ያበቀለ እንደሆነ ለማህበረሰቡ አይበጅም፣ ቢያድግም አባቱን የሚገፋ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም ገፊ (በአካባቢው አጠራር ሚንጊ ተብሎ) ይጣላል። ከዚህም በተጨማሪ ጥርስ እንደማብቀሉ ሁሉ መውለቁም ላይ ችግር አለ። በላይኛው የበቀለው ድዱ አሁንም ቀድሞ ከወለቀ ሚንጊ ተብሎ ይጣላል። የዚህ እምነት ሰለባ የሆኑ በርካታ ህጻናት ደግሞ ወደገደል እንዲጣሉ ሆነዋል።

ትደነቅ ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ በእሷ ላይ የደረሰ ባይሆንም በማሳደጊያው ውስጥ ግን መሰል ግፎች ሊፈጸሙባቸው ሲሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ከተረፉ በርካታ ልጆች ጋር ነው ያደገችው።ሁኔታውን ስታስረዳም እንዲህ ትላለች "...ሚንጊ (ገፊ) ተብለው ሊጣሉ ሊወረወሩ ከነበሩ በርካታ ልጆች ጋር በማደጌ ደስተኛ ነኝ።እንደውም እድለኛ ነኝም ብዬ አስባለሁ።እነሱን ማግኘቴ ብርታት ሆኖኛል።ምን ለማለት ፈልጌ ነው እኔና ወንድሞቼ ማሳደጊያ ድርጅት የገባነው ቤተሰቦቻችንን በሞት ስላጣን ነው፤ እነሱ ግን ቤተሰብ ኖሯቸው ገፊ ተብለው ሊጣሉ የነበሩ እንደ ክፉ እድል የተቆጠሩ ልጆች በመሆናቸው ነው ማሳደጊያ የገቡት፤ ይህ ደግሞ በእኔ ላይ ያጣሁትን ነገር እንዳላስብ አድርጎኛል " ትቀጥልናም ‹‹እኛ እግዚአብሔር ፈቀዶ ቤተሰቦቻችንን ወሰደ ፤ እነዚህ ልጆች



ፎቶ፦ ገበዮ ገብሬ

ትደነቅ ጉልዱ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ግን እነሱ ባልፈጠሩት ነገር በጎጂ ልማድ በማህበረሰቡ ኋላ ቀር አመለካከት ከቤተሰባቸው ጋር እንዳያድጉ ሆነዋል፤ በዚህም አንድ ላይ ተሰብስበን እኔ የእነሱ እህት ሆኜ እነሱ ደግሞ የእኔ እህትና ወንድም ሆነው እንድንኖር ሆነናል። ደስተኝነትን በጋራ ፈጥረናልም›› ትላለች ቤተሰብን መነጠቅ በአንድ ሞት ብቻ እንዳልሆነ ስታወሳ።

በሐመር ብሄረሰብ የሰው ልጅ የወተት ጥርሱን በታችኛው ማብቀል ሲገባው እንደ እርኩሳኑ በላይኛው ያበቀለ እንደሆነ ለማህበረሰቡ አይበጅም፤ ቢያድግም አባቱን የሚገፋ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም ገፌ (በአካባቢው አጠራር ሚንጊ ተብሎ) ይጣላል። ከዚህም በተጨማሪ ጥርስ እንደማብቀሉ ሁሉ መውለቁም ላይ ችግር አለ። በላይኛው የበቀለው ድዱ አሁንም ቀድሞ ከወለቀ ሚንጊ ተብሎ ይጣላል

### ጉዞ ወደ ዩኒቨርሲቲ

ትደነቅ ምንም እንኳን ወላጆቿን ገና በጨቅላ እድሜዋ ብታጣቸውም የታናናሽ ወንድሞቿ ሃላፊነት እሷ ላይ ቢጫንም በትምህርቷ ግን ለመበርታት በጣም ጥረት ታደርጋለች።ለዚህም ማሳያው የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈትና ያመጣችው ውጤት ነው።ጊዜው ፈታኝ ቢሆንም ውጤቷ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም አስገብቷታል።

"...የማትሪክ ውጤቴ ማማሩ በጣም ነበር ያስደሰተኝ፤ እድሌም ጥሩ ነበር መሰለኝ ከወንድሞቼ ሳልርቅ እማር ዘንድ እዛው ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተመደብኩ፤ ሁለተኛው ማሳደጊያ ድርጅቴም እንደ ቤተሰብ ክትትል ያደርጉልኛል።የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ያሟሉልኛል።እረፍት ሲሆን ሄጄ ከወንድሞቼ ጋር ተጫውቼ ወደ ዩኒቨርሲቲ እገባለሁ። በዚህም በጣም ደስተኛ ሆኜ ለመማር በቅቻለሁ" በማለትም የዩኒቨርሲቲ ቆይተዋ ምን እንደሚመስል ትናገራለች፡፡

ትደነቅ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ባታውቅም ከልጅነቷ ጀምሮ ኮምፒውተር የመጠቀም ብቻም አይደለም የመቅረብ ፍራቻ ነበረባት።ይህ ሁኔታ ደግሞ በጓደኞቿ ዘንድም ማሾፊያ አድርጓታል።ይህንን ችግሯን ለመረዳት ግን የመረጠችው የትምህርት መስክ ኮምፒውተር ሳይንስን ነበር።እናም የምትፈራውን ኮምፒውተር አብራው መዋል ጀመረች።አልፋ ተርፋም ስለምንነቱና ምን እንደሚጠቅም ሁሉ አብጠርጥራ አወቀች።በዚህም በጣም ደስተኛ ከመሆኗም ባለፈ የውጤት ችግር ሳይገጥማት መካከለኛ በሆነ ውጤት ተመረቀች፡፡

"...የሚያሳድገን ድርጅት በተለይም ከከተማ ወጣ ብለን የሰውን አኗኗር፣ ባህሉን፣ ወጉን ፣ ምርቱን፣ ምን አለ የለም የሚለውን እንድናይ ሁልጊዜም ትምህርት ሲዘጋ ወደገጠር ይልከን ነበር።እኔም እድሉን ተጠቅሜ የአባቴን የትውልድ መንደር እየሄድኩ አይ ነበርና አካባቢው ላይ ለትምህርት የሚሰጠው በተለይም ሴቶችን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ የሚደረገው ጥረት በጣም ዝቅተኛ መሆኑንን ታዘብኩ" የምትለው ትደነቅ፤ አባቷ ነብሳቸውን ይማረውና በሱሪ ወረዳ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰው ነበሩ።እሷ ደግሞ የእሳቸው ልጅ ናት።ስለዚህም በጎ ተጽዕኖ ለመፍጠር ችላለች።ለዚህ ያገዛት ደግሞ አባቷን የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎች ሁሉ መጣች ብለው መሰብሰብ መቻላቸውና የእርሷን ሃሳብ መቀበላቸው ነው።

እሷም የተማረችውን እያጣቀሰች ሴትን ልጅ ማስተማር አገርን ማስተማር፣ ቤተሰብን መለወጥ እንደሆነ ደጋግማ ትነግራቸዋለች።በዚህም የአባቷን ፈለግ ተከትላ በማህበረሰቡ ዘንድ በጎ አመለካከትን ፈጥራለች።ይህ ማህበረሰብ ደግሞ በውስጡ አንዲት የተማረች ለግላጋ ሴት ልጅ ማግኘቱ በጣም አስደስቶታል።በዚህም አካባቢውን ወክላ ድምጽ ትሁንልን ብለው ተመኝተዋታል።እናም ትደነቅ የመጨረሻ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን እየተከታተለች ባለችበት ወቅት የሱሪ ወረዳን ወክላ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤትን ትቀላቀል ዘንድ እጩ አደረጓት።

"...የአካባቢው ሰው እኔን በእጩነት እንዳቀረበኝ ስሰማ በጣም ነው የደነገጥኩት።ለመደንገጤ ደግሞ ዋናው ምክንያት የተማርኩት ትምህርትና ፖለቲካው አይገናኝም።ከዚያ በፊትም ስለ ፖለቲካ ትኩረት አድርጌ የሰራሁት ነገር የለም።እንደውም ሊሆን የማይችል ነገር ነው ብዬ ሁሉ ተከራከርኩ።ነገር ግን ያመነኘን የተማመነብኝን ሕዝብ እምቢ ማለት ከበደኝ።ይህ እንቢታ ደግሞ በራሱ የሚያመጣው ቅሬታ ከባድ እንደሚሆን ታሰበኝ።ስለዚህም ምንም እንኳን ሃላፊነቱ በጣም ከባድ ቢሆንም ተቀበልኩት" ትላለች፡፡

ትደነቅ ይህንን ትልቅ ሃላፊነት ስትቀበል ሌላም ምክንያት ነበራት። በተለይም እሷን አይተው ሴት ህጻናት ወጣቶች በትምህርት እንዲተጉ ለማድረግ፤ ወላጆችም ማስተማር እንዲችሉ ለማበረታታት ነው።መማር ለካ እንዲህ ያስከብራል እንዲሉ ትፈልጋለችና ነው።የወቅቱ አሳዳጊ አባቷም ብርታቷ ስለነበሩ ለማድረግ አስወስኗታል።በተለይም የእርሳቸው ‹‹ትችያለሽ፣ ትወጪዋለሽ ፣ አይዞሽ በርቺ›› በማለት የሰጧት ድጋፍ ብርታቷ ሆኖላታል። እናም ኃላፊነቱን ተቀብላ ወደስራው ገብታለች። ትምህርቷን እንዳጠናቀቀችም በቀጥታ ወደ ተመደበችበት የህዝብ እንደራሴ ምክር ቤት ሄዳለች፡፡

### ወጣቷ የሱሪ የሕዝብ እንደራሴ

ትደነቅ አምኗት ለመረጧት ማህበረሰብ ትልቅ ክብር አላት። የወላጅ አባቷን ተጽዕኖ ፈጣሪነት ሚናም በማስቀጠሏ ትልቅ ክብር ይሰማታል። አሁን ላይ የወገኖቿን ድምጽ በህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ውስጥ እያሰማች ትገኛለች። ይበጃል፣ ይጠቅማል የምትለውን ሃሳብም ትሰነዝራለች። ለማህበረሰቡ ወግናም ትሟገታለች። መደረግ ያለበት ነገር እንዲሆንም የማትቆፍረው ድንጋይ የለም።

የትደነቅ ህልም ተሰሚነቷንና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷን ተጠቅማ በተለይ በአካባቢዋ (በተመረጠችበት ቦታ ) ላይ ያሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲወገዱ ማስቻል፣ ሴቶች በብዛት ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት መሄድም ብቻ ሳይሆን ተምረው አገር የሚለውጡ ልጆች እንዲሆኑ መሥራት፤ ለአካባቢያቸው ሰዎች ሕይወት መለወጥ የበኩላቸውን የሚወጡ ዜጎችን መፍጠር ነው።

### ሁለቱ ታናናሽ ወንድሞቿ

ትደነቅ ከእናትና አባቷ ሞት በኋላ የሁለቱን ወንድሞቿን ሃላፊነት ወስዳ እንደ እህትም እንደ እናትም ሆና አሳድጋቸዋለች።ከእሷ ቀጥሎ ያለው ሳሙኤል ጉልዱ አሁን ላይ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እየተማረ ሲሆን የእሱ ታናሽ የቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ፍቃዱ ደግሞ ዘንድሮ የ11ኛ ክፍል ትምህርቱን በመማር ላይ ይገኛል።እስከ አሁንም ቢሆን የማሳደጊያ ድርጅቱ እየረዳቸው ነው፡፡

"...ወንድሞቼ ማሳደጊያ ውስጥ እንዳደጉ ልጆች አይደሉም።በጣም በጥሩ ሥነ ምግባር ያደጉ ራሳቸውን የሚያውቁ ጀርባቸው ላይ ማንም እንደሌላቸውና መማር ራሳቸውን ለማውጣት አይነተኛ መንገድ መሆኑን የተረዱ ናቸው።ለእኔም የሚያስቡልኝ ምርጥ ወንድሞች ሆነውልኛል።እነሱ ስላሉኝም በጣም ደስተኛ ነኝ።ለዚህ ያደረሰን ተቋምም ትልቅ ምስጋና ይገባዋል" ትላለች ጉዟቸው ዛሬ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ስታስረዳ።

### እሷም እናት ሆነች

ትደነቅ ያለ እናትና አባት ብታድግም የነበረችባቸው የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት እናትና አባት እንደሆኗት ታምናለች። በዚያ ላይ በጥሩ ሥነ ምግባር እንድታድግ አድርገዋታል። በትምህርቷም ጎበዝ የመሆኗ ምስጢር እነርሱ ናቸው። ዛሬ ላይ የሱሪ ማህበረሰብ ተወካይ በመሆን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተጣለባትን ሃላፊነት በአግባቡ እየተወጣች ለመገኘቷም መሰረት ሆነዋታል። ይህ ደግሞ ራሷን አይታ የራሷን ውሳኔ እንድትወስን አስችሏታል።ይህም አግብታ የልጅ እናት እንድትሆን የሚያደርግ ነው።እናም ከዚህ ሥራዋ ጎን ለጎን ጓደኛዋ ከነበረ ሰው አንድ ልጅ ወልዳ የእናትነት ሚናዋን እየተወጣች እንድትቀጥል እድሉን ሰጥቷታል።

‹‹...እኔም አድጌ ልጅ ወልጄ የሕይወትን መንገድ አንድ ብዬዋለሁ ፤ ስራዬን እየሰራሁ ልጄን እያሳደኩ ነው።አሁን ደግሞ ራሴን በተሻለ ሁኔታ አብቅቼ መገኘት ስላለብኝ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን እየተማርኩ ነው" ትላለች።

### መልዕክት

እንደ እኔና ወንድሞቼ ቤተሰቦቻቸውን በተለያየ ምክንያት አጥተው ለችግር የተጋለጡ ነገር ግን ትንሽ ድጋፍ ቢያገኙ ደግሞ አገርና ወገናቸውን መጥቀም የሚችሉ በርካታ ታዳጊ ህጻናት በየቦታው በዘመድ አዝማድ ቤት አሉ።እነዚህ ህጻናት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንጻር ሕይወታቸውን በማይሆን መንገድ እየኖሩ ነው።እኛ ደግሞ ቤተሰብ ብናጣም ሰብሳቢ ድርጅት በማግኘታችን እዚህ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሰናል። በመሆኑም መንግሥት እነዚህን ልጆች ሊያያቸው ይገባል። በተለይ ደግሞ ባለሀብቱ ቢያግዛቸው የበለጠ መስራት የሚችሉ ዜጎችን ማግኘት ይቻላል።

በተጨማሪም ህጻናትን ሰብስበው በበጎ ፍቃድ እያሳደጉ እያስተማሩ በጥሩ ሥነ ምግባር አንጸው ብቁ ዜጋ እያፈሩ ያሉ ድርጅቶች ተገቢን ትኩረትና ድጋፍ ቢያደርጉላቸው መልካም ነው።ሥራቸውም ደስታቸውም ሊቆጠር የማይችል ይሆናልና።ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን የጎዳና ተዳዳሪዎችን እናበራክታለን።እንዲሁም በየቤቱ አምራች ሊሆኑ የሚችሉ ታዳጊና ወጣቶችን ማፍራት ይሳነናል። ስለሆነም እድል ያላገኙ ልጆችን እንመልከታቸው፤ ለህጻናት ማሳደጊያ ድርጅቶች ልዩ ድጋፍና ክትትል እናድርግላቸው በማለት መልዕክቷን አስተላልፋለች።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## የ ‹‹ማይስ›› ቱሪዝም ኢንዱስትሪ - የቱሪዝም ዘርፉ ሌላኛው አቅም

**ዳግም ከበደ**

‹‹ማይስ›› ቱሪዝም በዓለማችን ላይ ከፍተኛ ገቢን የሚያንቀሳቅስና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተመራጭ እየሆነ የመጣ ንኡስ የቱሪዝም ዘርፍ ነው። ይህ የቱሪዝም ዘርፍ በሆቴልና ሆስፒታሊቲ፣ ዓለም አቀፍ ስብሰባ፣ ለማበረታቻና ሽልማት የሚካሄዱ የተቋማት ስብሰባዎች እንዲሁም ወቅትን ጠብቀው በሚካሄዱ የንግድ ኤግዚቢሽኖች ላይ የሚያተኩር የቱሪዝም አይነት ነው።

ያደጉ አገራት ከመስህብ ቱሪዝም በተጨማሪ ምጣኔ ሀብታቸውን በሚደግፈው በዚሁ ግዙፍ ኢንዱስትሪ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው እየሰሩ ይገኛሉ። እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2017 የተካሄደ ዓለም አቀፍ ጥናት ማይስ ቱሪዝም አንድ ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያንቀሳቅስ ግዙፍ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ መሆን ችሏል። ጥናቱ ይህ አሃዝ እስከ 2025 (ከሁለት ዓመታት በኋላ) ወደ አንድ ነጥብ 5 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር እምደሚመነደግ ቅድመ ግምቱን አስቀምጧል። ከዚህ መረዳት የምንችለው የሆቴል፣ ኮንፍረንስ፣ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንዲሁም ልዩ ልዩ የማይስ ቱሪዝም ንኡሶችን የሚይዘው ኢንዱስትሪ ለዓለማችን የምጣኔ ሀብት ምንጭ እንደሆነ ነው።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫና የልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ቢሮዎች ያሉባት የአፍሪካ መዲና ነች። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ለማይስ ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ምቹ መናሃሪያ ያደርጋታል። ዘርፉ በዋናነት የጉባዔ፣ የአውደ ርእይና ባዛር፣ የንግድ ውይይትና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ዋና ማጠንጠኛው በመሆኑ አገሪቱ ምጣኔ ሀብቷን እንድታሳድግ፣ ተመራጭ የስብሰባ ቱሪዝም ከተማ እንድትሆንና ያንን ተከትሎ ዜጎች በሚፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ እድል ይሰጣል።

የማይስ ቱሪዝም ፅንሰ ሃሳብ ትግበራ ካለፉት 10 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ ይገኛል። መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎም የማይስ ኢትዮጵያ የኮንቬንሽን ቢሮም በይፋ ተመስርቷል፡፡ ይህ ቢሮ ኢትዮጵያን ከዓለም አቀፍ ጉባዔዎች እና ሁነቶች የቱሪዝም ተጠቃሚ ለማድረግ ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ ከሁለት ዓመት በፊት ምስረታው በፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እና የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እና የቱሪዝም ኢትዮጵያ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ይፋ በተደረገበት ወቅት ተናግረው ነበር።

ፕሬዚዳንቷ በወቅቱ ኮንቬንሽን ቢሮ መመስረቱ ታሪካዊ መሆኑን በመጥቀስ በአግባቡ ከተሰራበት ለውጥ እንደሚያመጣ አስታውቀዋል። ቢሮው በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ የመጣውን የማይስ ቱሪዝም ወይም የጉባኤ፣ የጉዞ ማበረታቻ፣ ኮንፈረንሶች፣ ሁነቶች እና አውደ ርዕዮችን መሰረት ካደረገው ቱሪዝም ኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንድትሆን እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በማይስ ቱሪዝም ላይ በግልም ሆነ በመንግሥት ተቋማት ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም፣ የሚፈለገውን ያህል ግን ውጤት ማምጣት እንዳልተቻለ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። አበረታች የሆኑ እርምጃዎች ይኑሩ እንጂ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጠቀሜታን ይዞ የሚመጣውን ይህን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ የሚደረገው ጥረት አሁንም በርካታ ሥራዎች እንደሚጠብቁ ነው እነዚሁ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስገነዘቡት።

አቶ ቁምነገር ተከተል ይባላል። የኦዚ ቢዝነስና ሆስፒታሊቲ ግሩፕ አማካሪ ድርጅት ዳይሬክተር ነው። በስብሰባ (ኮንፈረንስ) ኢንዱስትሪው ላይ ለዓመታት ሰርቷል። እርሱ አገራት ኢንዱስትሪውን በየራሳቸው መንገድ እንደሚተረጉሙት ይናገራል። አንዳንዶቹ ከማይስ ቱሪዝም አውደ ርእይና ባዛርን በመውሰድ የትኩረት ማእከል ለመሆን፤ ሌሎች ደግሞ በስብሰባና መሰል የኢንዱስትሪው ክፍሎች ላይ በማተኮር እንደሚሰሩ ይገልፃል።

“ቱሪዝምን በመዝናኛ ዘርፍ ማለትም የመስህብ ስፍራዎችን ማስጎብኘት እና በማይስ ቱሪዝም ልንከፍለው እንችላለን” የሚለው አቶ ቁምነገር፣ አሁን አሁን አገራት ትላልቅ ማእከላትን በመክፈት ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች በአገራቸው እንዲደረጉ በመሳብ በቱሪዝም ዘርፉ ገቢን የማስገኛ ዘዴን መፍጠር እንደቻሉ ይገልፃል። ለመዝናኛ ጉዳይ ከሚደረገው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ጋር ሲነፃፀርም “ማይስ” ወይም የስብሰባ ቱሪዝም የተሻለና ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም እያስገኘላቸው እንደሆነ ያመለክታል።

MICE Ethiopia

Meet in the Land of Origins



ይህም በአሃዝ ሲሰላ ከመዝናኛ ቱሪዝሙ የ 300 እና 400 እጥፍ ገቢ እንደሚያስገኝ መረጋገጡን ያስረዳል።

አቶ ቁምነገር ኢትዮጵያ ባለፉት ስምንት እና ዘጠኝ ዓመታት በማይስ (ስብሰባ) ቱሪዝም ላይ ትኩረት አድርጋ እንድትሰራ ሲጎተጉቱ መቆየታቸውን ያስታውሳል። የኮንቬንሽን ቢሮ እንዲቋቋም በዋናነት ምክረ ሃሳብ በማቅረብ መሳተፉንም ይገልጻል። ጥረቱ ተሳክቶም ይህ ተቋም ወደ ስራ መግባት መቻሉን ተናግሮ፣ ቢሮው በዋናነት እንዲሰራ የታቀደው በገበያ ልማት ላይ እንደሆነም ያስረዳል።

“እንዲህ አይነት ተቋማት መመስረታቸው ብቻ ሳይሆን ለመስሪያ ቤቱ ተገቢውን በጀት መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል” የሚለው አቶ ቁምነገር፤ ዓለም አቀፍ የገበያ ስራ ለመስራት በቂ በጀት መኖሩ አስፈላጊ እንደሆነም ይገልፃል። አሁን አሁን በትላልቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት እየተሰሩ ያሉት ጅምር የማስተዋወቅ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥሉ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመልክቶ፣ ይህም ኢትዮጵያ የስብሰባ ቱሪዝም በስፋት የሚካሄድባት ተመራጭ ሀገር እንድትሆን እንደሚያግዝ ያስረዳል።

በተለይ የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት ምቹ ከሆኑ ኢንዱስትሪዎች መካከል ቀዳሚውና የተሻለው (መጭበርበር የሌለበት) የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት የማይስ ቱሪዝም መሆኑን ዳይሬክተሩ ይናገራል፡፡ ለእዚህም አንደኛው ዋንኛው ምክንያት ይህን መሰል ሁነት የሚያዘጋጁት ግዙፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መሆናቸውን በመጥቀስም ክፍያዎች ያለምንም ውስብስብ መንገድ ወደ አገር ካዝና እንዲገባ የሚያደርግ መሆኑን አስታውቋል። በሁለተኝነት አገር ከማይስ ቱሪዝም ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነች ለማወቅና ትክክለኛ መለኪያ ለማግኘት ተመራጭ ኢንዱስትሪ እንደሆነም ጠቁሟል።

“በአገራችን አሁን ያለው አሰራር አያስኬድም” የሚለው አቶ ቁምነገር፤ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን አሁን ካለበት መንገድ በተሻለ መምራት እንደሚያስፈልግ ይገልፃል። በአዲስ አበባ እየተካሄደ የሚገኘውን 36ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እንደ ምሳሌ አንስቶ “እስካሁን ይህንን አቅም ለመጠቀም ምን የተለየና አዲስ አካሄድ አምጥተናል?” በማለት ጥያቄ ያነሳል። ከሆቴሎች ኪራይ ውጪ ከዚህ ቀደም ምንም አይነት ተጨማሪ ገቢ አገሪቱ እያስገኘች አልነበረም ይላል፡፡

የአፍሪካ ህብረት ስብሰባን ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ እንግዶችን ከማይስ ቱሪዝም አንፃር ኢትዮጵያን ተጨማሪ ጥቅም በምን መልኩ ማስገኘት ይቻላል? በሚል ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ ቁምነገር ሲመልሱ “ አዳዲስ የማይስ ቱሪዝም ጥቅሎችን በማዘጋጀት ከስብሰባው ውጪ በከተማዋ ያሉ የመስህብ ስፍራዎችን ከማስጎብኘት ጀምሮ በርካታ ስራዎችን መስራት ይቻላል” በማለት ምላሹን ይሰጣል።

በተለይ አዳዲስ ሁነቶችን ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ በመቅረፅ በዚያ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባም ጠቁሞ፣ በግል በመኪና ኪራይም ሆነ በልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪነት የተመዘገቡ የግል ድርጅቶች በዚህ ወቅት የአፍሪካ ህብረት ስብሰባን ተከትሎ የሚገኘን የውጭ ምንዛሬ በቀጥታ ሪፖርት የሚያደርጉበት ሥርዓት በመዘርጋትና አገር ተጠቃሚ እንድትሆን መስራት እንደሚገባም ያሳስባል።

በተጨማሪ የመሪዎች ስብሰባ በሚደረግበት ወቅት ከፍተኛ የደህንነት ጥንቃቄ እንደሚደረግ ጠቅሶ፣ ገቢ የሚያስገኙ ሁነቶችም የዚያኑ ያህል በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እንደሚገባም ምክረ ሃሳብ ይሰጣል።

“በዓለም ላይ ከፍተኛ የስብሰባ ቱሪዝም ከጤናና ከኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚመጣ ነው” የሚለው አቶ ቁምነገር፤ አገራት ከዚህ ተጠቃሚ ለመሆን ተወዳዳሪና ጨረታዎችን የማሸነፍ አቋም ሊገነቡ እንደሚገባም ይመክራል። ከዚህ በተጨማሪ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች በኢትዮጵያ ሲካሄዱ ውጤቱን መለካት እንደሚያስፈልግ እና የተገኙ ስኬቶችም ሆኑ የታዩ ችግሮችን ገምግሞ ከዚያ ትምህርት መውሰድ እንደሚያሻ አስገንዝቧል።

ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችንና ባዛሮችን እያሰናዳች ትገኛለች፤ ከዚህ ውስጥ የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ከልዩ ልዩ የመንግሥት ተቋማት ጋር በትብብር “17ኛውን የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባዔ” በስኬት አዘጋጅቶ ማጠናቀቁ ይታወሳል። ሌላው የአፍሪካ ህብረት የስራ አስፈፃሚዎች ጉባኤን ጨምሮ የመሪዎች ጉባኤና በየደረጃው የሚካሄዱ ስብሰባዎችን እንደ ህብረቱ መቀመጫነቷ በየጊዜው ታካሂዳለች። ይሄ ደግሞ ከስብሰባ ቱሪዝም እድገትና ከዚያም ለሚገኘው ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ የራሱ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል።

በአዲስ አበባ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ እየተካሄደ የሚገኘው የህብረቱ ሀገሮች የመሪዎች ጉባዔም ከዲፕሎማሲያዊ ድሉ ባሻገር ኢትዮጵያ በሆስፒታሊቲው ዘርፍ ትልቅ ጥቅም የምታገኝበት እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የቱሪዝም ሚኒስቴር ልዩ ልዩ የቱሪዝም ጥቅሎችን በማዘጋጀት በኢትዮጵያ የሚገኙ መሪዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ ሚኒስትሮችና ሌሎች የተቋሙ ሰራተኞች በኢትዮጵያ ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ እና የከተማዋን መዳረሻዎች እንዲጎበኙ እየሰራ መሆኑን አሳውቋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት የህብረቱን ጉባኤ አስመልክተው ለመገናኛ ብዙሃን እንደገለጹት፤ ለመሪዎች ጉባዔ ታዳሚዎች ከአቀባበል ጀምሮ በጥሩ መስተንግዶ ቆይታቸው አስደሳች እንዲሆን ዝግጅት ተደርጓል። ለጉባዔው ተሳታፊዎች የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማስተዋወቅና እንዲጎበኙ ለማድረግ አስጎብኚዎችና ሆቴሎች ዝግጁ ሆነዋል፡፡

የጉባዔው ተሳታፊዎች በከተማዋ የሚገኙ የቱሪዝም መስህቦችን የሚያውቁበትና ለመጎብኘት መረጃ የሚያገኙበት አዲስ መተግበሪያ ዝግጁ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታዋ አስታውቀዋል፡፡ መተግበሪያው በመዲናዋ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ የመዝናኛ ሥፍራዎችንና አጠቃላይ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ገጽታ የሚያስተዋውቁ መረጃዎችን የያዘ እንደሆነ ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በመግቢያችን ላይ ለማንሳት እንደሞከርነው የማይስ ቱሪዝም በዓለማችን ላይ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ድርሻ ያለው ግዙፍ ኢንዱስትሪ ነው። በኢትዮጵያ ይህንን ኢንዱስትሪ ለማስፋፋት በትኩረት መስራት ከተቻለ በርካታ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያም ትልቅ አቅም እንዳላት ይታመናል።

በአዲስ አበባ በቅርብ ዓመታት ተገንብተው ለበርካታ ቱሪስቶች መዳረሻ የሆኑትን አንድነት፣ እንጦጦ እና ወዳጅነት ፓርኮችን ጨምሮ ሌሎች ቱሪስቶች ሊጎበኟቸው የሚችሉ ብዙ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችም አላት። በዚህ ላይ የስብሰባ ቱሪዝም (ማይስ ቱሪዝም) ፅንሰ ሃሳብን ማስፋትና የሆስፒታሊቲ ዘርፉን ማሳደግ ከተቻለ ከማይስ (ስብሰባ) ኢንዱስትሪው የሚገኘውን ሀብት ልክ እንደሌሎቹ አገራት መቋደስ ይቻላል።

36ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤና ከጉባኤው ጎን ለጎን የሚካሄዱት በርካታ መድረኮች እየተገባደዱ ናቸው፡፡ ጉባኤው በአዲስ አበባ ቢያንስ በአመት አንዴ የሚካሄድ እንደመሆኑ ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በማይስ (ስብሰባ) ቱሪዝም ላይ በሚገባ በመስራት ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው የበለጠ ተጠቃሚ መሆን ይገባል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# የካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ

ዋስልኝ አየለ



የየካቲት ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተለይም በታሪክና ፖለቲካ ጉልህ ሚና ያለው ወር መሆኑን ባለፈው ሳምንት ጠቅሰናል፡፡ ከእነዚህ የየካቲት ወር ጉልህ ታሪካዊ ክስተቶች የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን እና ዓድዋ በደማቁ የሚታወሱ ናቸው፡፡ ዓድዋን በቀኑ ስንደርስ እናስታውሰዋለን፡፡

ለዛሬው ግን ከ86 ዓመታት በፊት ልክ በዛሬዋ ቀን የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ስለተከሰተው የሰማዕታት መታሰቢያና መነሻ ሰበቦቹን እናስታውሳለን፡፡

በ1888 ዓ.ም በዓድዋ ላይ ዓለም አቀፍ ውርደትን የተከናነበው ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ያኔ የደረሰበት ሽንፈት ሲያንገበግበው ከኖረ በኋላ በ1928 ዓ.ም በቀሉን ሊወጣ ዳግም ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

እነሆ ከ85 ዓመታት በፊት በዛሬዋ ቀን የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም እንዲህ ሆነ። ከጣሊያን ንጉሣዊ ቤተሰቦች አንድ ልዑል ልጅ በመወለዱ በኢትዮጵያ ድል ያለ ድግስ ተዘጋጅቶ እንዲከበር በጀኔራል ግራዚያኒ ትዕዛዝ ተላለፈ። ዝግጅቱም በቀድሞው የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ቅጥር ግቢ ውስጥ የፋሽስቱ ባለሥልጣናት እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው ሁሉ እንዲገኙ ተደረገ።

በዚህ ዝግጅት ላይ ትልቅ የደስታ ስጦታ መዘጋጀቱን አብርሃም ደቦጭ ሰማ። ውሳኔውንም ለበጅሮንድ ለጥይበሉ ገብሬ፣ ለብላታ ዳዲ፣ ለቀኝ አዝማች ወልደዮሃንስ፣ ለደጅ አዝማች ወልደ አማኑኤል እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጓደኞቹ ተናገረ። ጥሪው ከተደረገበት ቦታ ማንም ሰው መሄድ እንደሌለበትም አስታወቃቸው። ዳሩ ግን የፋሽስቱ እንዲህ በአገራቸው ላይ ደጋሽ እና ጋባዥ መሆን ያላንገበገባቸው ሆድ አደሮች ‹‹ዞር በል ወዲያ›› ብለውት ለመሄድ ወሰኑ። አብርሃምም ለቅርብ ጓደኛው ለሞገስ አስገዶም ከነገረው በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መከሩ። በዚች ታሪከኛ ቀን የካቲት 12 ከማንም ቀድመው ዝግጅቱ ላይ መገኘት እንዳለባቸውም ወሰኑ።

ከመሄዳቸው በፊትም እንዲህ አደረጉ። በአብርሃም ደቦጭ ቤት ውስጥ የጣሊያንን ባንዲራ በሳንቃ ወለል ላይ አንጥፈው ሚስማር ገደገዱበት። የጣሊያን ፋሽስት ጉዱን አላየ! እዚያ ሽር ጉድ ይላል። አብርሃም እና ሞገስም የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ወደ ዝግጅቱ ገቡ።

ግራዚያኒም በአዳራሹ እየፈነጠዘ ብሉልኝ ጠጡልኝ ይል ጀመር። አዳራሹ ውስጥ ታድመው ዝግጅቱን ከሚያደምቁ አድር ባዮች ውስጥ ግን፤ የድግሱ ምግብ እሬት እሬት ያላቸው፣ አዳራሹ የፋሽስት ሶላቶ መራገጫ መሆኑ ያንገበገባቸው የአገር ነፃነት የናፈቃቸው ሁለት ወጣቶች ነበሩ። ሞገስ አስገዶም እና አብርሃም ደቦጭ። ገዳይ ቢያረፋፍድ ሟች ይገሰግሳል ነውና ነገሩ፤ ግራዚያኒ ከሚገባው በላይ ቅጡን አጣ። በአዳራሹ የታደመውን ሰው እየዞረ ለተወለደው ልጅ ስም እንዲያወጡ ጠየቀ። አድር ባይ ባንዳ ሁሉ ስም ያወጣ ጀመር። አሁን የአብርሃምና የሞገስ ትዕግስት አልቋል። ለማንም የፋሽስት ዲቃላ ማነው ስም የሚያወጣ ተባባሉ። በቃ አሁን ጉድ ሊፈላ ነው። በኪሳቸው ደብቀውት የነበረውን ቦንብ መዥረጥ፣መዥረጥ አደረጉት። ግራዚያኒ ላይ ተወረወረ። ቆስሎም ወደቀ። ለአሸሸ ገዳሜ የታሰበው አዳራሽ ‹‹ዋይ! ዋይ!›› ተባለበት።

የጣሊያን ፋሽስቶች በእልህ እና በብስጭት ከሰላሳ ሺህ በላይ ኢትዮጳያውያንን በግፍ ጨፈጨፉ፡፡ አብርሃም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶምም ወደ ሱዳን እየሄዱ ሳሉ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ተገደሉ፡፡ ከዚያ በኋላ እንግዲህ የኢትዮጵያ ቆራጥ አርበኞች ጣሊያንን ከአገር ለማስወጣት ሴት ወንድ ሳይሉ በዱር በገደሉ መዋጋት ጀመሩ፡፡ እነ ሸዋረገድ ገድሌ እና ከበደች ሥዩም ከሴት አርበኞች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የሞገስ አስገዶምና የአብርሃም ደቦጭ ቁርጠኛ ውሳኔ ብዙ ጀግኖችን ለትግል አነሳሳ፡፡ በኋላም ለእናት አገራቸው ቆርጠው በተነሱ አርበኞች ትግል የጣሊያን ፋሽስት ጓዙን ጠቅልሎ ከኢትዮጵያ ወጣ፡፡ እነዚህ ጀግኖች አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው እነሆ ኢትዮጵያን ብቸኛ አፍሪካዊት ነፃ አገር አስብለዋታል፡፡

ጣሊያኖች ደጋግመው የሞከሩት ሙከራ በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከሽፏል፡፡ ጣሊያን በ1879 ዓ.ም ዶጋሌ ላይ፣ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ደግሞ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ ሽንፈትን አስተናግዳለች፡፡ ይህ ሁሉ የኢትዮጵያ ድል ነው፡፡ በመጨረሻም በየካቲት 12 ሰማዕታት ምክንያት የኢትዮጵያ አርበኞች ዳግም የአገራቸውን ነጻነት አስጠበቁ፡፡ ለዚህም መታሰቢያ ከአምስት ኪሎ ከፍ ብሎ ስድስት ኪሎ ሳይደርስ የሚገኘው የካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ተገነባ።

በጭፍጨፋው ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎችን ለመዘከር የካቲት 12 በብሔራዊ ደረጃ እንዲዘከር በ1934 ዓ.ም ታወጀ፡፡ በ1951 ዓ.ም ደግሞ አሁን የምናየው እና 28 ሜትር ርዝመት እንዳለው የሚነገረው የሠማዕታት መታሰቢያ ሐውልት እንዲቆም ተደርጓል።

የነገሩን ሥረ መነሻ ካየነው ከዓድዋ በፊትም ቆየት ያለ ነው፡፡ አውሮፓውያን የአፍሪካ አገራትን ለመቀራመትና የቅኝ ግዛት ለማድረግ አይናቸውን ወደ አፍሪካ ያማተሩበት የታሪክ ምዕራፍ ነበር፡፡ በወቅቱ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት በአውሮፓውያን እጅ ሲወድቁ፣ ኢትዮጵያን ለመውረር ቀይ ባሕርን ያቋረጠችው ጣሊያን ግን ሳይሳካላት ቀርቷል፡፡ በነጮቹ የእርስ በርስ ተባባሪነት ተደጋጋሚ ሴራ ቢሞክሩም ኢትዮጵያ ላይ ግን ሊሰራ አልቻለም፡፡

ይህ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲከሽፍ ቆይቶ በ1888 ዓድዋ ላይ የኢትዮጵያን ገናናነት ከፍ አድርጎ ያሳየው ታላቁ የዓድዋ ድል ተመዘገበ፡፡ በጦርነቱም፤ የጣሊያንን ጦር የገጠመው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጣሊያንን በማሸነፍ ድል ማስመዝገቡ፣ ድሉ የዓለም ጥቁር ድል ሲባል ጣሊያን የሽንፈት ካባ ተከናንባ የኢትዮጵያን ምድር ለቃ ወጣች።

በዚህ በዓድዋ ሽንፈት ቂም የያዘችው ጣሊያን ከ40 ዓመታት የሰፌ ዝግጅት በኋላ ተመልሳ በመምጣት ኢትዮጵያን በመውረር ብዙ አትዮጵያውያንን ለመስዋዕትነት በመዳረጓ የዛሬው የየካቲት 12 መታሰቢያ ሆነ፡፡ የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ከፍተኛ ዝግጅት ስታደርግ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ግን ከፍተኛ መዘናጋት ነበር፡፡ በሕዝቦቿ ጀግንነትና አይበገሬነት ድል ማድረግ ተቻለ እንጂ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የነበረው ሁኔታ የታሰበበት አልነበረም።

በተለይም ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ህልፈት በኋላ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ ካየነው ደግሞ እንደ ሰገሌ አይነት የእርስ በርስ ጦርነቶችና ሽኩቻዎች የነበሩበት ነው፡፡ አልጋ ወራሹ ተፈሪ መኮንን ንጉሠ ነገሥት እስከሚሆኑ ድረስ የነበሩ ሁኔታዎችም ወጣ ገባ ያሉ ነበሩ፡፡ ይፋዊው የጣሊያን ወረራ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ መንበረ ሥልጣናቸውን ካረጋጉ በኋላ መሆኑ ግን የተሻለ ሳያደርገው አይቀርም፤ ምክንያቱም ንጉሡ ብዙ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራታቸው ይነገርላቸዋል፡፡

ይፋዊው የጣሊያን ወረራ ከመጀመሩ ጊዜ ደግሞ የዓለም መንግሥታት ማህበር (League of Nations) የተመሰረተበት ነበር፤ ኢትዮጵያ ለዚሁ ማህበር ወረራው ተገቢ አይደለም በማለት በንጉሷ በኩል አቤት ብትልም አጋርነት ካሳዩ ጥቂት ሀገራት ውጭ ሰሚ አላገኘችም ነበር።

ይሁንና የዓለም መንግሥታት ማህበር (league of nations) ከተመሰረተ ከዓመታት በኋላ ጣሊያን በድጋሚ ኢትዮጵያ ለመውረር ጦርነት ጀመረች፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና አርበኞች አገርን ላለማስደፈር ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል።

ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ የጣሊያንን ድርጊት አዲስ ለተቋቋመው የመንግሥታት ማህበር ለማመልከት ወደ ውጭ አገራት ቢሄዱም ሕግና ሉዓላዊነት በወቅቱ ትኩረት ሊሰጣቸው ስላልቻለ ኢትዮጵያውያን የነጻነት ተጋድሏቸውን አጠናክረው ቀጠሉ ማለት ነው። ስለዚህ የየካቲት 12 ሰማዕታት ጀግኖች እልቂት የዓለም ኢፍትሐዊነትና አድሎ የፈጠረው ጭምር ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን በጀግንነታቸው ቢኮሩበትም የዓለምን ኢፍትሐዊነት ግን ሲመሰክር ይኖራል፡፡

ለአፍሪካ አገራት ቅኝ ግዛት መነሻ የነበረውን የበርሊን ጉባኤ በጥቂቱ እናስታውሰው፡፡ ፖርቱጋል በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር 1884 በፖርቱጋል ጥያቄ መሠረት የጀርመን ቻንስለር ኦቶ ቮን ቢስማርክ ዋናውን የምዕራባዊ አገሮች ዓለም አቀፋዊ ስብሰባ በመሰብሰብ ጥያቄዎችን በማደራጀት በአፍሪካ አገሮች ቁጥጥር ላይ ተወያዩ፡፡

የበርሊን ኮንፈረንስ በተከፈተበት ጊዜ አሥራ አራት አገሮች በአምባሳደሮች ተገኝተዋል፡፡ በወቅቱ የተወከሉት አገሮች አስትሪያ ሃንጋሪ፣ ቤልጂየም፣ ዴንማርክ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ ጣሊያን፣ ኔዘርላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሩሲያ፣ ስፔን፣ ስዊድን፣ ኖርዌይ ቱርክ እና ዩናይትድ ስቴትስ ነበሩ፡፡ ከህዳር 1884 ጀምሮ ለሦስት ወራት በተካሄደው ውይይት በአውሮፓውያን ታላላቅ ኃይሎች መካከል የስብሰባዎች ስብስብ ነበር ፡፡ በድርድሩ ውስጥ የተሳተፉት አገራት ዋና ዓላማ የአፍሪካን ቅኝ ግዛት ለማስፈፀም ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ነበር።ከአስራ አራቱ አገራት መካከል ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ታላቋ ብሪታንያ እና ፖርቹጋል በወቅቱ የቅኝ ግዛት አፍሪካን ተቆጣጠሩት፡፡

በጉባኤው ጊዜ በአፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች የሚገኙት የአውሮፓ ኃያላን አገሮች ብቻ ነበሩ፡፡ በበርሊን ጉባኤ ላይ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የአፍሪካን አህጉራት ለመቆጣጠር እየተዋጉ ሁሉ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ከመዋጋታቸው ይልቅ ስምምነታቸው በልጦ አፍሪካን ተከፋፍለው ቅኝ ገዝተዋል፡፡ የአውሮፓ ቅኝ ገዥ አገራትና የአፍሪካ ቅኝ ተገዢ አገራት የሚከተሉት ነበሩ፡፡

ታላቋ ብሪታኒያ የኬፕ ኤይ ካይሮን ቅኝ ግዛቶች ለማግኘት የግብፅ፣ የታላቋ ሱዳን፣ ኡጋንዳ፣ ኬንያ (የብሪቲሽ ምስራቅ አፍሪካ)፣ ደቡብ አፍሪካ እና ዛምቢያ፣ ዚምባብዌ (ሩዴያ)፣ ቦትስዋና፣ ብሪታኒያ ናይጄሪያና ጋና (ጎልድኮስት) ገዝታለች፡፡

ፈረንሳይ በአብዛኛው ምዕራብ አፍሪካን፣ ከሞሪታኒያ እስከ ቻድ (ፈረንሣዊ ምዕራብ አፍሪካ) እንዲሁም ጋቦንና ኮንጎ ሪፖብሊክ (ፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ) ወስዳለች፡፡

ቤልጂየም እና ንጉስ ሌኦፖል ዴሞክራቲክ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ቤልጂየም ኮንጎ) ተቆጣጠሩት፡፡

ፖርቱጋል በምሥራቅና በምዕራብ ሞዛምቢክ ሞዛምቢክን ወሰደች፡፡ የጣሊያን ይዞታዎች ደግሞ ሶማሊያ (ጣሊያን ሶማሊላንድ) እና የኢትዮጵያ ክፍል ነበሩ፡፡

ጀርመን በናሚቢያ (ጀርመን ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ) እና ታንዛኒያ (ጀርመን የምስራቅ አፍሪካ) አግኝታለች። የአንዳንድ አፍሪካ አገራት ስሞች በቅኝ ገዥዎቻቸው ስያሜ የወጡ ናቸው፡፡ ቅኝ ገዢዎቹ የያዙትን ቦታ የራሳቸውን አገር መነሻ ስም ያደርጉታል፡፡ በተለይ እንግሊዞች ‹‹ብሪቲሽ...›› እያሉ ይሰይማሉ፡፡

ይህ ሁሉ አፍሪካን የመቀራመት ዘመቻ ነው እንግዲህ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ የከሸፈባቸው፡፡ ምንም እንኳን የሰሩት ሥራ ዛሬ ድረስ ያበለሻሸው ነገር ቢኖርም፤ ኢትዮጵያ ግን በራሷ ማንነት ብቻ የምትታወቅ የጀግና አገር እንዲትሆን አድርጓታል፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ እንደ የካቲት 12 አይነት የሰማዕታት ዋጋ ተከፍሎበት ነው፡፡

ክብር ለጀግኖች ሰማዕታት!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የኛ ሰው በናሳ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ብዙዎች ስለታላቁ የኢትዮጵያ ሊቅ ብዕራቸውን እያነሱና በቃላት እያሞካሹ ይከትቡለታል። የእውቀቱንም ጥግ እየጠቀሱ በዓለማችን ግዙፍ በሆነው የስፔስ ሳይንስ የምርምር ማዕከል ወይም ናሳ ውስጥ ስለሰሯቸው ስራዎችም በልበ ሙሉነት ይመሰክራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በተቃራኒው ይህ ሰው ምናባዊ የፈጠራ ትርክት እንጂ በናሳ ውስጥ በጭራሽ አልነበረም ብለው ሲከራከሩ ታይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ‹‹በናሳ ውስጥ ሊሰሩ ይቅርና በበሯ እንኳን አላለፉም›› የሚሉ ወገኖች ሙግት ገጥመው አይተናል፡፡ የዚህ ሰው አወዛጋቢ የናሳ ተመራማሪነትና ክርክር ያስነሳ ማንነት ብዙዎች ያላዩት በአመድ የተዳፈነ ፍም እሳት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያዊው የናሳ ሳይንቲስት ዶክተር ኢንጅነር ቅጣው እጅጉ።

የዚህ ሳይንቲስት ሕይወትና ታሪካዊ እውነታው ሚስጥር ለዘመናት ታፍኖ ከርሟል፤ ለምን? ምናልባትም የሰራበት የዓለማችን ትልቁ የሕዋ ምርምር ተቋም ናሳ ሚስጥራዊ ከመሆኑ የተነሳ? ወይንስ ከበስተጀርባው ሌላ ዓላማና ይዘት ያለው ታሪክ ይኖር ይሆን? አንዳንዶች እውነታውን መቀበል ለምን ከበዳቸው? የሳይንቲስቱ ጉዳይ ውስብስብ ሆኖ ከመቆየቱም ባሻገር በሁለት የተለያዩ ዓለማት ያሉ እውነታዎች አንዱ አንዱን በመርታት የእውነትን ዙፋን ላይ ለመቆናጠጥ እርስ በእርስ ሲፋጩ ቆይተዋል። በስተመጨረሻም ዙፋኑ የእውነተኛው እውነት ብቻ ነው። ብዙ የውሸት መቃብሮች አንዲትን እውነት የመቅበር አቅም የላቸውምና ያም ተባለ ይህ እውነታው ግን አንድና አንድ ብቻ ነው። ይሄውም ቅጣው እጅጉ ኢትዮጵያ ሀገራችን የምትኮራበት፣ የናሳ ሳይንቲስት ነበር። ለመሆኑ ይህ ሰው ከየት ተነስቶ የት ደረሰ፣ በሕይወት ዘመኑስ ለአገሩና ለዓለም ምንስ ማበርከት ቻለ፤ እውነታውን ተሞርኩዘን ዝናውን ጥግ ሳንከድ ስለ ሳይንቲስቱ ሕይወትና ስለ ተቀበሩ እውነታዎች ከብዙ በጥቂቱ እንመልከት፡፡ የዚህ ሳይንቲስት የታሪክ እውነታ ሲጀምርም እንዲህ ነበር። በዚሁ ወር የካቲት 16 ቀን 1948 ዓ/ም በደቡብ ኢትዮጵያዋ ቦንጋ ከተማ ውስጥ ከእናታቸው ወይዘሮ አስካለ በላይነህ እና ከአባታቸው ከአቶ እጅጉ ሀይሌ መወለዱን የሚገልፁ በርካታ መዛግብት አሉ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱንም በቦንጋ ዋከና ጀምሮ በጅማ ከተማ አጠናቀቀ። በዚህ ወቅት በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ከሌላው ተማሪ በተለይ ልዩ ፍላጎትና ወጣ ያሉ የፈጠራ ሙከራዎችን በግሉ ያደርግ እንደነበር በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች ይናገራሉ። በሒሳብ እና ፊይዚክስ እንዲሁም የኬሚስትሪ ትምህርቶች ላይ የተለየ ፍቅርም ነበረው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት በማጠናቀቅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በጅማ ከተማ ተከታተለ።

የዶክተር ኢንጂነር ቅጣው እጅጉ ቀጣዩ ህልም ወደ አውሮፓ ሀገራት በመሄድ ቀሪውን የትምህርትና የሕይወት ዘመኑን እዚያው መግፋት ነበር። ምክንያቱም ደግሞ የትምህርት ብቻ ሳይሆን ጠንካራ የሆነ የነጻነትና ትግል የፖለቲካ አቋም ስለነበረው ኑሮን በኢትዮጵያ ለመግፋት አስቸጋሪ ሆኖበት ነበር። ከዚህ በኋላም ወደ ጃፓን አገር በመሄድ በኦሳካ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋና የጃፓን ኢኮኖሚ፣ በሄሮሺማ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የኢንዱስትሪ እና የአውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ አጥንቶ አጠናቋል። በሀገረ ጃፓን በትምህርት ቆይታው በነበረው የተለየ ችሎታና ከዚያም ወጥቶ በሚሰራቸው የፈጠራ ስራዎች ከወደ አሜሪካን ሀገር ሌላ የትምህርት እድል እንዲያገኝ ረዳው። እዚያም በመሄድ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የሁለተኛ ዲግሪውን ተከታተለ። ቅጣው እጅጉ በሄደበት ሁሉ ተምሮ፣ እለት ከእለት የእውቀቱንም ማዕድ እየቆረሰ ጠግቤያለሁ የሚል ባለመሆኑ አብዝቶ የእውቀትን በር የሚያንኳኳና በስኬቱም የማይረካ የሕይወት ዘመን ተማሪ ነበር። በየሴኮንዱና በየደቂቃው አዳዲስ እውቀትን መሸመትም የሕይወት ፍልስፍናው ነው። ይህም ጥረቱ ለብዙዎች ህልም ሆኖ ወደሚቀረውና ጥቂት የዓለማችን ልሂቃን ብቻ ወደሚገቡበት ወደ ታላቁ የናሳ ግቢ ሰተት ብሎ እንዲገባ አድርጎታል፡፡



ዶክተር ኢንጅነር ቅጣው እጅጉ

በናሳ ውስጥ ባደረገው ቆይታ በሁለት አበይት ዘርፎች በርካታ የምርምር ስራዎችን ማበርከት ችሏል። በዚህም በሲስተም መሃንዲስነትና በጠፈር ሳይንቲስትነት በመቀጠር የናሳ ጉዞውን ጀመረ። ከሌሎች መሃንዲስ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን ለእኛ ዓለምና ለሌሎች ፕላኔቶች የምርምር ስራ የሚረዱ የጠፈር ላይ መንኩራኩሮችን መፍጠር እንደቻለም የፅሁፍ ማስረጃዎች አሉ፡፡ የሰው ልጅን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጠፈር በወሰደው አፖሎ 11 መንኩራኩር ላይም አሻራውን አሳርፏል። ለአንዳንዶች ውሸት እስከሚመስል ድረስም ከፈጣሪ በተሰጠው ልዩ ችሎታና እውቀት በናሳ ውስጥ ሁለት የኤሮ-ስፔስ መወርወሪያ ሜካኒዝምን ለግዙፉ የአውሮፕላን ማምረቻ ለቦይንግ ኩባንያ ለመስራትም በቅቶል። ኔክስት ጀኔሬሽን የተሰኘውን ዓለምአቀፍ ሳተላይትን ከፈለሰፉት ሳይንቲስቶች መካከል አንደኛው ዶክተር ኢንጂነር ቅጣው እጅጉ ስለመሆኑም ይነገራል፡፡ ሌላው ደግሞ ‘ትራንስ ቴክ ኢንተርናሽናል’ በመባል የሚታወቀውን ድርጅት መስራች ጭምር መሆኑ ነው።

አንዳንድ እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ይሄ ትርክት እንጂ ቅጣው የሚባል ሳይንቲስት የለም ሲሉ መደመጣቸው እጅጉን የሚያስገርምም የሚያሳዝንም ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ የቴክኖሎጂና የመረጃ ዘመን ስለዚህ ሳይንቲስት እውነታውን አለማወቅ አንድ ነገር ሆኖ ሳለ ውሸት ነው ብሎ ሽንጥን ገትሮ መከራከር ግን ትልቅ ስህተት ነው። እንደሚባለው የዚህ ሳይንቲስት ታሪክ ምናባዊ የፈጠራ ትርክት አይደለም። ለዚህ እውነታ በቂ ማስረጃዎች ማግኘት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህልም የናሳ ሳይንቲስቶች በሚሞቱበት ወቅት ታሪካቸው የሚሰፍርበት የበይነ መረብ ባህረ መዝገብ አለው። በዚህ መዝገብ ላይም ዶክተር ኢንጂነር ቅጣው እጅጉ በናሳ ውስጥ በስፔስ ሳይንስ ዲፓርትመንት የጀት ፕሮፔልሽን ተመራማሪ ሳይንቲስት እንደነበር ከስራዎቹ ጋር አጣምሮ አስቀምጦታል። ይህንንም መረጃ አስደግፎ ሎሳንጀለስ ታይምስ የተሰኘው ታዋቂ ጋዜጣ፣ በፈረንጆቹ ጥር 18/2006ዓ.ም የሳይንቲስቱን ግለ ታሪክ ይዞ ወጥቷል።

‹‹ዶክተር ቅጣው እጅጉ በብዙዎች ዘንድ የተወደደ፣ በትህትናው የተመሰገነ ፣ በስራው የተደነቀ፣ በራዕዩ ብዙ ተከታዮችን ያፈራ፣ የብዙዎች ተስፋና አርዓያ እንዲሁም ለአገሩ ትልቅ ኩራት ነው›› ሲልም የነበረውን ስብእና ሳይቀር ይገልጸዋል። ሌላው ደግሞ ይህንን እውነታ የሚያረጋግጡልን በዓለም ባንክ፣ በናሳ እና በሌሎች ድርጅቶች የታተሙ ዶክመንቶች በግልጽ ተጽፈው ይገኛሉ። ለምሳሌ ከናሳ ዶክመንቶች አንዱ በ 1980 ነበር የተዘጋጀው። በዚያ ዘመን ኢንጂነር ቅጣው ‘ጀት ፕሮፖሉዥን ላብራቶሪ’ ውስጥ ይሰራ እንደነበር ይገልጻል።

ታዲያ አንዳንዶች ይህን የገሀድ እውነታ አምኖ መቀበል ስለምን ከበዳቸው? እውነታው የጥቂቶች ሳይሆን የዓለም ሁሉ ነው። ይህ እውነት ካልሆነ ነጮቹ ያውም ስለአንድ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ስለምን ብለው ይጽፉታል? ጉዳዩን የውሸት አድርገው በየማህበራዊ ሚዲያው የሚያራግቡ አንዳንድ አካላትን እንመለከታለን። የእነዚህ አካላት ትልቁ ዓላማም የሳይንቲስቱንና የአገርን ታሪክ አጠልሽቶ ሆዳቸውን የሚሞሉበትን ጊዜያዊ እንጀራ ከማግኘት የዘለለ አይደለም። በእነርሱ የውሸት አደባባይ እኛም ተከትለን ከዞርን የዋህነት ብቻ ሳይሆን ሞኝነትም ጭምር ነው። የሳይንቲስቱን ብቻ ሳይሆን አገራችን ኢትዮጵያ በናሳ ውስጥ ስሟን ያሰፈሩበትንም ታሪክ ጥላሸት መቀባትና ማደብዘዝ ይሆናል።

ሳይንቲስቱ የኢህአዴግ መንግሥት ኢትዮጵያን ይመራ በነበረበት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በወቅቱ አገሪቱን ይመሩ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አቀባበል እንዳደረጉላቸው የሚጠቁሙ መረጃዎችም አሉ፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይም ቁጭ ብለው መነጋገራቸውን የሚገልፁ ሰነዶችም አሉ፡፡ ታዲያ የእውነትም ሳይንቲስት ካልነበሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ተታለው ነበር ማለት ነው? እንዴት አንድ ሰው ያልሆነውን ነኝ በማለት ዓለምን ሁሉ ሊያታልል ይችላል?

የዶክተር ኢንጂነር ቅጣው እጅጉን ማንነት ከትንሿ የቦንጋ ምድር እስከ አሜሪካው ናሳ ድረስ ሙሉ የሕይወት ታሪካቸውን የሚያስቃኝ ‘ልጃችን’ የተሰኘ ዶክመንተሪ ፊልም በመስራት ሰኔ 20 ቀን 2007 ዓ/ም በሚሊኒየም አዳራሽ ለእይታ በቅቶ ነበር። ፊልሙ የ40 ደቂቃዎች ያህል ቆይታ ያለው ሲሆን እጅጉ ቅጣው ማን ነበሩ፣ ምንስ ሰሩ፣ በአጠቃላይ ከሕይወት ዘመን በቆይታቸው እስከ ህልፈተ ሞታቸው ድረስ የነበረውን እውነታ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ፊልሙን ለመስራት ለሁለት ዓመታት ያህል ልዩ ጥናት የተካሄደ ሲሆን ይህንንም ሰርቶ ለማጠናቀቅ 1.5 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል። ከፊልሙ የተገኘው ገቢም ለአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ መልክ ተበርክቷል።

ሌላው አከራካሪው ጉዳይ የሳይንቲስቱ አሟሟት ነው። አንዳንዶች ‹‹ቅጣው እጅጉ የናሳ ሳይንቲስት በመሆናቸው ሲያገለግሏት የቆየችው አሜሪካን ብዙ ሚስጥሮች እንዳይወጡባት ስትል በስተመጨረሻ የሞትን ጽዋ አስጎነጨቻቸው›› ሲሉ ሌሎች ደግሞ ‹‹ከወደ ኢትዮጵያ በነበራቸው የፖለቲካ አቋም ምክንያት ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ መንግሥት ነው የተገደሉት›› በማለት ሲሞግቱ ይደመጣሉ። አሁንም ግን እውነታው የትኛውም አይደለም።

ቅጣው እጅጉ ከሰራው በላይ እንዳይሰራ፣ ከናሳው ደጅ ላይ ስሙ ከወጣው በላይ እንዳይወጣ በሕይወቱ ላይ የተጋረጠ አንድ ትልቅ ችግር ነበረ። ቅጣው የልብ ህመም ታማሚ ነበር። በዚህ ላይ የቅርጫት ኳስን አብዝቶ ይወድ ነበር። ታዲያ በአንድ ወቅት ወደ ሁስትን ቴክሳስ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ሄዶ በፈረንጆቹ ጥር 13 ቀን 2006 እንደ ወትሮው የቅርጫት ኳስ ተጫውቶ ከዘመዶቹ ቤት ተመለሰ። መታጠቢያ ቤት በመግባትም ሰውነቱን ታጥቦ እንደተመለሰ ያቺ መጥፎ ሰዓት ደረሰች። ሰውነቱ በድካም ራደ። ልቡም እየደከመ ሄዶ በስተመጨረሻም ነብሱን ከትልቅ እውቀት ጋር የሰጠው ፈጣሪ በ58 ዓመቱ መልሶ ተቀበላት። ይህም የሶስት ልጆቹ እናትና የትዳር አጋሩ ስቴላ እንዲሁም የቅርብ ወዳጆቹ የሚናገሩት ብቸኛው እውነታ ነው። በአንድ ሰው ታሪክ ውስጥ ሁለት አይነት ውሸቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ፈጽሞ ግን ሁለት አይነት እውነታ አይኖርምና ብቸኛው እውነትም ቅጣው እጅጉ በናሳ ውስጥ የነበረ ኩሩ የኢትዮጵያዊ የኛ ሰው መሆኑ ነው።

# ዓለም አቀፍ



## በሶሪያ በጥቂቱ 53 ንጹሃን በታጣቂዎች ተገደሉ

ጥቃት የደረሰበት ሆምስ የተባለው አካባቢ ከዚህ ቀደም የአይ ኤስ ዋነኛ ይዞታ እንደነበር የሚታወስ ነው። በሶሪያ በታጣቂዎች በተከፈተ ተኩስ በጥቂቱ 53 ንጹሃን መገደላቸው ተገልጿል። በማዕከላዊ ሆምስ ግዛት ለተፈጸመው ጥቃት የአይ ኤስ ታጣቂዎች ተጠያቂ ተደርገዋል።

የሶሪያው ብሄራዊ የዜና ወኪል ሳና እንደዘገበው፥ ንጹሃኑ ለምግብነት የሚውሉ ፍራፍሪዎችን ሲለቅሙ ነው ጥቃቱ የተከፈተው። በተከፈተው ተኩስ ጉዳት የደረሰባቸውን ሁሉም ሰዎች ወደ ፓልሜራ ሆስፒታል ቢወሰዱም የተረፉት ጥቂቶቹ ናቸው ብሏል ዘገባው። አምስት ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ የገጠማቸውም ወደ ሌላ ሆስፒታል እንዲዛወሩ ተደርጎ ህክምና እየተደረገላቸው ይገኛል።

አንድ ከጥቃቱ የተረፈ ግለሰብ የአይ ኤስ ታጣቂዎች ተኩስ እንደከፈቱባቸው መናገሩን ሬውተርስ ዘግቧል። አይ ኤስ ግን እስካሁን ለጥቃቱ ሃላፊነቱን እንደሚወስድ አላስታወቀም። ንጹሃኑ የተገደሉበት ግዛት ሆምስ ከዚህ ቀደም በአይ ኤስ ይዞታ ስር ከነበሩ አካባቢዎች የሚጠቀስ ነው። ከዓመታት በፊት አብዛኛውን የሶሪያ ክፍል ይዞ የነበረው አይ ኤስ ከሶስት ወገን በሚደርስበት የማጥቃት እርምጃ ከበርካታ ይዞታዎቹ ለቋል።

በሩሲያ የሚደገፉ የበሽር አል አሳድ መንግሥት ሃይሎች በአንድ ወገን፥ የሶሪያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ደግሞ በአሜሪካ እየተደገፉ በቡድኑ ላይ ኪሳራ አድርሰዋል። በቱርክ መንግሥት የትጥቅ ድጋፍ የሚደረግላቸው ታጣቂዎችም በአይ ኤስ ላይ ጥቃት ማድረሳቸውን ቀጥለዋል። በዚህም ቡድኑ የአጥፍቶ መጥፋትንና ፈጣን ጥቃት አድርሶ ማምለጥን ተያይዞታል።

12 ዓመት በሆነው የሶሪያ የእርስ በርስ ጦርነት ከ500 ሺህ በላይ ሰዎች እንደተገደሉ መረጃዎች ያሳያሉ፤ ከ6 ሚሊዮን በላይ ሶሪያውያንም ሀገራቸውን ለቀው ለመሰደድ ተገደዋል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

## በፕሬዚዳንት ማክሮን ላይ ጥቃት ሊፈጽሙ ነበር የተባሉ ቀኝ አክራሪዎች ተፈረደባቸው



በፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሲያሴሩ ነበር የተባሉ ሦስት የቀኝ አክራሪ ቡድን አባላት ጥፋተኛ ተብለው ተፈረደባቸው። ግለሰቦቹ በ2018 (እአአ) ፕሬዚዳንቱ ይገኙበታል በተባለው የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት መታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ላይ በቢላ ጥቃት ሊፈጽሙባቸው አቅደው ነበር ተብሏል።

የተከሳሾቹ ጠበቆች ደንበኞቻቸው ግልጽ ዕቅድ የሌላቸው፣ ግራ የተጋቡ ጽንፈኞች ናቸው በማለት ለፍርድ ቤቱ ተናግረዋል። የፈረንሳይ ዐቃቤ ሕግ ግን ጥቃቱን ሊፈጽሙ ሲያሴሩ የነበሩት ጽንፈኛ ግለሰቦች በኃይል መንግሥትን የመገልበጥም ፍላጎት ነበራቸው ሲል ከሷቸዋል።

ጉዳያቸውን ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት ሦስቱ ተከሳሾች የሽብር ድርጊት ለመፈጸም በመዘጋጀት ሴራ ጥፋተኛ ሆነው እንዳገኛቸው ገልጿል። በዚህም ከተከሳሾቹ መካከል የ66 ዓመቱ ጃን ፒየር ቡየር ከፍተኛው ቅጣት ተበይኖበታል። ወንጀሉ እስከ 10 ዓመት የሚደርስ እስር የሚያስቀጣ ቢሆንም፣ ግለሰቡ በአንድ ዓመት ገደብ የአራት ዓመት አስር ተፈርዶበታል። ሌሎቹ ሁለት ተከሳሾች ግን የአጭር ጊዜ የእስር ቅጣት ብቻ ተላልፎባቸዋል።

ሌላ አራተኛ ሰው ደግሞ የጦር መሳሪያ በመያዝ በቀረበበት ክስ በገደብ የስድስት ወራት እስር ተፈርዶበታል። ሁሉም ተከሳሾች የተያዙት በፈረንሳይ ምሥራቃዊ ክፍል በምትገኘው ሞዜል ክልል ውስጥ ነው። ፖሊስ በቦየር መኪና ውስጥ ኮማንዶዎች የሚጠቀሙበት አይነት ቢላ እና የወታደሮች ጃኬት ያገኘ ሲሆን፣ እንዲሁም ቤቱ ውስጥም ሽጉጦች ተገኝተዋል።

ሌሎች ዘጠኝ የጽንፈኛ የቡድኑ አባላት ከቀረበባቸው ክስ በነጻ ተሰናብተዋል። የቡድኑ አባላት በኢንተርኔት ላይ በተደረጉ የዘረኝነት ውይይቶች ላይ ስለስደት፣ የእርስ በርስ ጦርነት ስጋት እንዳላቸው እና ለፕሬዚዳንት ማክሮን ስላላቸው ጥላቻ የተናገሩት በፍርድ ሂደቱ ወቅት በችሎቱ ተደምጧል። በአንደኛው ውይይት ላይ ሦስት ልጆች ያሏት እናት፣ በ500 የሩሲያ ወታደሮች በመታገዝ በአገሪቱ ፕሬዚዳንት ቤተ መንግሥት ላይ ጥቃት መሰንዘር ስለሚቻልበት ሁኔታ ስትናገር ተደምጣለች።

በተጨማሪም ቡድኑ በመስጂዶች እና በስደተኞች ላይ ጥቃቶችን ለመፈጸም በማሴር እንደተጠረጠሩ ተገልጿል። አንዲት የ55 ዓመት ተከሳሽ ስለሰነዘረችው ሙስሊሞችን የማገት እና የማቃጠል ሃሳቧን በተመለከተ በፍርድ ቤቱ ተጠይቃ “ተበሳጭቼ እና ተቆጥቼ ስለነበረ፣ ይህንን ተናግሬ ሊሆን ይችላል” ብላ መልሳለች።

ዋናው ዐቃቤ ሕግ ጽንፈኛው ቡድን “የአመጽ ድርጊቶች መፈልፈያ” ነው በማለት፣ አመለካከታቸውም “ከተለመደው ወጣ ያለ” እና “የሚደቅኑት አደጋም ተጨባጭ ነው” በማለት ከሰዋል። የተከሳሾቹ ጠበቃ ግን ቡድኑ አባላት ትኩረት ያላገኙ እና ከገጠር አካባቢ የመጡ የፀረ መንግሥቱ የቢጫ ጃኬት ለባሾቹ እንቅስቃሴ ደጋፊዎች ናቸው ብሏል። ጨምሮም በቡድኑ አባላት “የጥላቻ” ንግግር መንጸባረቁን ተቀብሎ፣ ነገር ግን ይህ ስሜት በገጠማቸው ማኅበራዊ ችግር ምክንያት የተፈጠረ ነው መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል።

ይህ ጽንፈኛ ቡድን የተመሠረተው ከስድስት ዓመት በፊት ጂሃዲስቶች አማካይነት እዚያው ፈረንሳይ ውስጥ በቻርሊ ሄብዶ መጽሔት እና የባታክላን የኮንሰርት አዳራሽን ጨምሮ በሌሎች ስፍራዎች ጥቃት ከፈጸሙ በኋላ ነበር።

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

**ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ጋር**
**በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም**

# የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ እድሎች እና ተግዳሮቶች

**በፍቅረተስፋዬ**

ከአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ጋር በተያያዘ እድሎች እና ተግዳሮቶች አንፃራዊ ትስስር አላቸው። የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እድሎችን የመጠቀም አቅም ሲያድግ ተግዳሮቶችን የማሳነስ እድል ይኖራል። እድሎች እና ተግዳሮች በአሠራር ሂደቱ በተግባር የታዩ ወይም ያጋጠሙ ሊሆኑ ይችላሉ። እኛም በዛሬው ትምህርታዊ ጽሁፋችን የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ እድሎች እና ተግዳሮቶችን እንደሚከተለው በወፍ በረር ልናስቃኛቹህ ወደናል። መልካም ንባብ!

**የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ እድሎች**

የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ለአያሌ እድሎች መከፈቻ ነው። በመጀመሪያ የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ዋጋ ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም መብቶቹ በባህሪያቸው ልዩ ናቸው። ስለዚህ ለመብቶች የሚደረግ ጥበቃ የፈጠራ ሥራዎችን በብቸኝነት ለመገልገል፣ የገበያተወዳዳሪነትን ለመቆጣጠር፣ ትርፋማ የገቢ ምንጮችን ለመያዝ፣ የእውቀት ግብይት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ለመሆን፣ አዳዲስ የንግድ አሠራር እድሎችን ለማየት እና ለማስፋት ያስችላል። ይህ ብቻ አይደለም፤ አእምሯዊ ንብረት ወሰን የሌለው የሰው ልጅ የመፍጠር ችሎታ ውጤት ስለሆነ የሕዝብ ቁጥር ብዛት፣ የመሬት መጥበብ፣ የጥሬ ሀብት ዕጦት ወይም የካፒታል ፈሰስ ማነስ ስጋት ሳይሆኑ ለሰው ልጅ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት ትልቅ ድርሻ አለው ማለት ይቻላል። ይህን በተረዳ መልኩ ለአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ሕግ እና ተቋማዊ የመብት አስተዳደር ማኖር እና በመስኩ የተፈጠረው ዓለምአቀፋዊ ትስስር እና በዚሁ ሳቢያ ከበርካታ ክልላዊ እና ብሔራዊ አቻ የአእምሯዊ ንብረት ተቋማት ጋር አብሮ የመሥራት ልምድ ዋጋው ብዙ ነው ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ እና ንግድ ትስስር ያላትን ቦታ እንድታይ ቢያንስ እድሎች ተከፍተዋል። አሁን ትልቁ ጥያቄ የተገኙትን እውናዊ እና እምቅ እድሎች እንዴት እንጠቀምባቸው የሚለው ነው። የጥያቄው መፍቻ መልካም አጋጣሚዎች ሳይባክኑ በቅብብሎሽ የመጠቀም አቅማችንን ማሳደግ እና ተግባር ላይ ማዋል ነው። በሌላ አነጋገር እድሎችን አሟጦ ለመጠቀም በአንፃሩ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን የመለየትና እንደየባህሪያቸው መፍትሄ መስጠትም አስፈላጊ ይሆናል።

**የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ተግዳሮቶች**

ለአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ተግዳሮቶች የገበያ እና የፋይናንስ እጦት፣ የመብት ጥሰቶች፣ ደካማ የመብት ማስከበር እና የመብት አስተዳደር ተዘውትረው የሚነሱ ናቸው። የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስናይም እነዚሁ ተግዳሮቶች የአሠራራችን ማነቆዎች ሆነው እናገኛቸዋለን።

የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ተቋማት የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የመገልገል እድሎችን ያመቻቻሉ። ነገር ግን ለሥራዎቹ የገበያ እና የፋይናንስ አቅርቦት ዋስትና አይኖራቸውም። አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን የፈጠራ ሥራዎችን እድገት በመናፈቅ ይመስላል “ባለሥልጣን መሥሪያቤቱ እየመዘገበ የፈጠራ ሠራተኛው ግን ተጠቃሚ ሲሆን አይታይም” የሚል ትችት ሲዘነዝሩ ይስተዋላል። ነገር ግን አንድ የአእምሯዊ ንብረት መብት በሕጉ ጥበቃ እስካገኘ ድረስ ሥራውን ተግባራዊ ለማድረግም ሆነ በገበያው ስኬታማ ለመሆን በዋናነት የመብቱ ባለቤቶች ጥናትና ጥረት ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። የበለጠ ትኩረት የሚሻው ችግር ግን በመረዳትም ይሁን ባለመረዳት የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ችግር ነው።

የአእምሯዊ ንብረት መብት ጥሰቶች ሕጉ ከሚሰጣቸው መብቶች አንፃር የሚመዘኑ ናቸው። መብቱ ጥበቃ ያገኘውን ፈጠራ ወይም ሥራ ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ ሌሎ ችሰዎች ንግድ ነክ ለሆኑ ተግባራት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሠሩበት፣ እንዳይጠቀሙበት፣ እንዳያከፋፍሉ ወይም እንዳይሸጡ ለመከልከል የተሰጠነው። በአንፃሩ ይህን መብት የሚጻረር ድርጊት መፈጸም የመብት ጥሰት ነው። የመብት ጥሰት ጥያቄም የሚነሳው ጥበቃ የተደረገለት መብት በተጣሰ ጊዜ ነው።

በአእምሯዊ ንብረት የመብት ጥሰት ችግሮችን የከፉ የሚያደርጋቸው እነሱን የመቆጣጠር አቅማችን ፈጣን በሆነው ቴክኖሎጂ ለውጥ ጭምር ስለሚፈተን ነው። ከቴክኖሎጂው መርቀቅ መለስም ቢሆን በአእምሯዊ ንብረት መብት ጥሰቶች ላይ የፍትህ አካላት ግንዛቤ አናሳ መሆን የችግሩ ትልቁ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል። ይህም ለአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል። ለአብነት ከቅጅ መብቶች ጋር በተያያዘ በአንድ የሰበር መዝገብ የኢኮኖሚ መብት ጥሰት በደረሰ ጊዜ የሞራል ጉዳትም ይኖራል ተብሏል።

“መጽሐፍት እንዲታተምልኝ በሰጠሁት ውል በተጠሪ ድርጅት ሰራተኛ ተሠርቆ በተሸጠብኝ መጽሐፍ ምክንያት ኪሣራ ደርሶብኛል፤ በአዋጅ ቁጥር 410/96 የተመለከተው የሞራል ካሣና ሳይሸጡ የቀሩ መጽሐፍት ዋጋ ይከፈለኝ” ብሎ አመልካች ላቀረበለት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ “የመብት ባለቤት በሕጉ ያሉት መብቶች ኢኮኖሚያዊና የሞራል መብቶች ናቸው” ብሎ ከኢኮኖሚያዊ መብቶች አንዱ ተጥሶ በተገኘ ጊዜ የሞራል ጉዳት ጥሰት ይኖራል።” የአመልካችም መብት በተጠሪ ተጥሷል”ብሎ ለደረሰው የህሊና ጉዳት ሞራል ካሣ በአዋጅቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) መሠረት አንድ መቶ ሺህ ብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል ብሏል። የውል ተቀባይ ድርጅት ሠራተኛ የፈጸመው ሕገወጥ ድርጊት የቅጅ መብት ጥሰት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው እንተውና የኢኮኖሚ መብት ጥሰት በደረሰ ጊዜ የሞራል መብት ጥሰት ይኖራል የመባሉን ተገቢነት እንይ።

በመብቶች ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ የሚወሰነው ሕጉ ጥበቃ ያደረገላቸው መብቶች ተጥሰው በተገኙ ጊዜ ነው። የሚካሰውም ሞራላዊ ጉዳት ወይም ቁሳዊ ጉዳት ነው። በመዝገቡ ተጥሷል የተባለው መብት ኦሪጂና ልሥራን ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሳየት የኢኮኖሚ መብት ነው ተብሏል። የሞራል መብትን በተመለከተ አዋጁ ጥበቃ ካደረገላቸው የሞራል መብቶች ውስጥ አንዳቸውም እንኳ በግልፅ ጥሰት ተፈጽሞበታል አልተባለም። ታዲያ በምን ሳቢያ የሞራል ጉዳት ካሣ ክፍያ ይገባል ተባለ? የሕጉን ዓላማ ስናይ “የኢኮኖሚ መብት ጥሰት በደረሰ ጊዜ የሞራል ጉዳትም ይኖራል” ተብሎ መፍትሄ የተሰጠበት አግባብ”የሕጉን መንፈስ የተከተለነው”ለማለት አያስችልም።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያና የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና

**ቦጋለ አበበ**

የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና በዓለም አትሌቲክስ ስር ከሚካሄዱ ውድድሮች በአንጋፋነቱ እና በፈታኝነቱ የሚጠቀስ ነው። እኤአ ከ1973 ጀምሮ የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናው ለ38 ጊዜያት በየዓመቱ ሲካሄድ የነበረ ሲሆን፤ እኤአ ከ2011 ወዲህ ግን በየሁለት ዓመቱ የሚደረግ ሆኗል። ይህም የሆነበት ምክንያት በተለይ ባለፉት 25 ዓመታት የምስራቅ አፍሪካ አትሌቶች በየውድድሩ እስከ 10 ያለውን ደረጃ በመቆጣጠር ያሳዩት የበላይነት ባስከተለው ጫና ነው።

በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያ በተሳትፎ ታሪኳ ታላላቅ ውጤቶችን አስመዝግባለች። በኦሊምፒኮችና በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ታላላቅ ስኬት ያገኙ አትሌቶች የተገኙትም ከፈታኙ የአገር አቋራጭ ሩጫ እንደሆነ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው እንዳላት ስኬት አስተናጋጅ ለመሆን አልታደለችም። በአንፃሩ ኬንያ ቻምፒዮናውን በማስተናገድ የመጀመሪያዋ ምስራቅ አፍሪካዊት አገር ናት።

ዩጋንዳን፣ ሞሮኮ ለሁለት ጊዜያት በ1975 እና በ1998፤ ደቡብ አፍሪካ በ1996 እንዲሁም ኬንያ በ2007 የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናውን አዘጋጅተዋል። ከአውሮፓ እንግሊዝ፤ ፖላንድ፤ ፈረንሳይ፤ ስፔን፤ ፖርቱጋልና ጣልያን ከአንድ ጊዜ በላይ ውድድሩን ያስተናገዱ ከተሞች ሲሆኑ፤ አሜሪካም ከአንድ ጊዜ በላይ አዘጋጅ ነበረች። ከኤስያ ጃፓን፤ ከመካከለኛው ምስራቅ ጆርዳን ሁሉ የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናን አስተናግደዋል። በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና የተሳትፎ ታሪክ ከፍተኛውን ውጤት በማስመዝገብ የምትጠቀሰው ኢትዮጵያ ውድድሩን የማዘጋጀት እድሏ ሰፊ ቢሆንም አልተሞከረም ወይም አልተሳካም።

የዓለም አትሌቲክስ ከ1 ዓመት በፊት ዘንድሮ በአውስትራሊያ ከሚካሄደው ቻምፒዮና በኋላ ቀጣዮቹን አስተናጋጅ አገሮች አስታውቋል። በ2024 45ኛውን ቻምፒዮና የአውሮፓዋ ክሮሽያ ስታስተናግድ፤ በ2026 ደግሞ 46ኛውን ቻምፒዮና አሜሪካ ታዘጋጃለች።

ኢትዮጵያ ባለፉት 43 ዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናዎች 275 ሜዳሊያዎችን ሰብስባለች። በ2019 በዴንማርክ አርሁስ የተካሄደው 43ኛው የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናም የኢትዮጵያ ቡድን በ5 የወርቅ በ3 የብርና በ3 ነሐስ በአጠቃላይ በ11 ሜዳልያዎች ሰብስባ ከዓለም አንደኛ ደረጃን ማግኘቷ ይታወሳል።

የኢትዮጵያ በቻምፒዮናው የተሳትፎ ታሪክ በአዋቂዎች ምድብ የአጭርና ረጅም ርቀት ውድድሮች ድርብ የወርቅ ሜዳልያዎች በማግኘት የመጀመሪያው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ነው። ቀነኒሳ በአጭር ርቀት 4 ኪሎ ሜትርና በረጅም ርቀት 12 ኪሎ ሜትር ውድድሮች በ5 ቻምፒዮናዎች በተከታታይ በማሸነፍ ብቸኛው አትሌት ሲሆን እኤአ በ2008 በረጅም ርቀት 6ኛውን የወርቅ ሜዳልያ በማግኘቱ ደግሞ በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮናው ታሪክ ከፍተኛውን የውጤት ክብረወሰን ያስመዘገበ አትሌት ሆኗል። በሌላ በኩል በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና በአዋቂዎች ምድብ ውጤታማ ከሆኑ የኢትዮጵያ ሴት አትሌቶች መጠቀስ ያለባቸው ደራርቱ ቱሉ፤ ጌጤ ዋሚ፤ ጥሩነሽ ዲባባ፤ ወርቅነሽ ኪዳኔ ዋናዎቹ ናቸው። ደራርቱ ቱሉ በረጅም ርቀት ለ3 ጊዜያት ያሸነፈች ሲሆን፣ ጥሩነሽ ዲባባ ደግሞ በአዋቂዎች ምድብ በረጅም ርቀት ለ3 ጊዜያት እንዲሁም በአጭር ርቀት 1 ጊዜ በማሸነፍ ከኢትዮጵያ ሴት አትሌቶች ትልቁን ውጤት አስመዝግበዋል።

በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና የመጀመሪያውን የሜዳልያ ያስመዘገበው ኢትዮጵያዊ አትሌት በአዋቂዎች ምድብ በወንዶች የ 12 ኪሎ ሜትር ውድድር መሐመድ ከድር ያስመዘገበው የብር ሜዳልያ ሲሆን ጊዜው እኤአ በ 1981 ነው። አትሌት መሐመድ ከድር ከዓመት በኋላም በ1982 በተመሳሳይ ረጅም ርቀት አሸንፎ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳልያ ለኢትዮጵያ አስገኝቷል። በአዋቂ ወንዶች የ 12 ኪሎ ሜትር ውድድር ኢትዮጵያ ከሰበሰበቻቸው 10 የወርቅ ሜዳልያዎች ስድስቱን ያስመዘገበው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ሲሆን እኤአ ከ2002-2008 በተካሄዱት የዓለም ቻምፒዮናዎች ነው። ሌሎቹን 4 የወርቅ ሜዳልያዎች ደግሞ መሐመድ ከድር (በ1982 እ.ኤ.አ)፣ በቀለ ደበሌ (በ1983 እ.ኤ.አ)፣ ገብረእግዚአብሔር ገ/ማርያም (በ2009 እ.ኤ.አ) እንዲሁም ኢማና መርጋ በ2011 እ.ኤ.አ ላይ አስመዝግበዋል።

በአዋቂ ሴቶች የ 8 ኪሎ ሜትር የረጅም ርቀት ውድድር ደግሞ በኢትዮጵያዊ አትሌት የመጀመሪያ ሜዳልያ የተገኘው እኤአ በ1991 ደራርቱ ቱሉ በወሰደችው የብር ሜዳልያ ነው። የመጀመሪያው የወርቅ ሜዳሊያ ደግሞ እኤአ በ1995 ላይ አሁንም ደራርቱ ቱሉ የተጐናፀፈች ሲሆን ሌሎች ሁለት የወርቅ ሜዳልያዎችን ደግሞ በ1975 እና በ2000 ማሳካት ችላለች። በአዋቂ ሴቶች ኢትዮጵያ ካስመዘገበቻቸው 9 የወርቅ ሜዳልያዎች 3 ከጥሩነሽ ዲባባ (በ2005፣በ2006፣ በ2008 እ.ኤ.አ) 2 በጌጤ ዋሚ (በ1996፣ በ1999 እ.ኤ.አ) እንዲሁም በወርቅነሽ ኪዳኔ (2003 እ.ኤ.አ) ተገኝተዋል።

በርካታ የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና ሜዳሊያዎችን በግል እና ከቡድን ጋር በማግኘት በወንዶች ቀነኒሳ በቀለ በአጠቃላይ 27 ሜዳሊያዎችን በመውሰድ ከዓለም አንደኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ፣ በሴቶች ደግሞ ኢትዮጵያዊቷ ወርቅነሽ ኪዳኔ በ21 ሜዳሊያዎች መሪነቱ ላይ ተቀምጣለች። በግልና በቡድን የወርቅ ሜዳሊያዎች ድምር የዓለም አገር አቋራጭን የተቆጣጠሩትም ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው። በወንዶች በግል ያገኛቸውን 12 ወርቅ ሜዳሊያዎች እና በቡድን ያገኛቸውን አራት የወርቅ ሜዳሊያዎች ጨምሮ በ16 ወርቅ ሜዳሊያዎች ቀነኒሳ በቀለ መሪነቱን ሲይዝ፣ በሴቶችም በግሏ አምስት፣ በቡድን ዘጠኝ የወርቅ ሜዳሊያዎችን ያገኘችው ጥሩነሽ ዲባባ በ 14 ወርቅ ሜዳሊያዎች በሴቶቹ ምድብ አንደኛነቱን ይዛለች። በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና የተሳትፎ ታሪካቸው ቢያንስ አራት ሜዳሊያዎችን በማግኘት ሰባት የኢትዮጵያ አትሌቶች ክብረወሰኑ አላቸው። እነሱም ሃይሉ መኮንን፣ ጌጤ ዋሚ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ወርቅነሽ ኪዳኔ፣ ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም፣ ጥሩነሽ ዲባባ እና መሰለች መልካሙ ናቸው።




## ልጆች ስለሰማእታት ቀን ምን ያህል ያውቃሉ

**በስጦሻቸው ልዑልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ ሳምንቱ እንዴት ነበር? እንደተለመደው ሳምንቱን በትምህርት እና በጥናት እንዳሳለፋችሁ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም እናንተ ጊዜያችሁን በአግባቡ የምትጠቀሙና በትምህርታችሁ የማትደራደሩ መሆናችሁን ስለማምን ነው።

ልጆች ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ተወርተው የማያልቁ በርካታ የጀግንነትና የሰማዕትነት ታሪኮች ያሏት በርካቶች የሚመኟት ውድ ሀገር ናት። ከእነዚህ በርካታ ታሪኮች መካከል ዛሬ በመከበር ላይ ያለው የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን ታሪክ አንዱ ነው። ልጆች ስለሰማዕታት ቀን ምን ያህል ታውቃላችሁ? በዛሬው ፅሁፋችን ስለ ሰማዕታት ቀን ታሪክና ለምን እንደሚከበር እነግራችኋለሁ።

በ1879 ዓ.ም ዶጋሌ ላይ፣ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ደግሞ የካቲት 23 ቀን በ1888 ዓድዋ ላይ የጣሊያንን ጦር የገጠመው የኢትዮጵያ ሠራዊት በማሸነፍ ድል አስመዝገበ፣ ድሉ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ድል ተብሎ የኢትዮጵያ ዝና በዓለም ናኘ። ጣሊያንም የሽንፈት ካባ ተከናንባ የኢትዮጵያን ምድር ለቃ ወጣች። የጣሊያን ዓድዋ ላይ መሸነፍ ያበሳጫቸው አውሮፓውያን ሀገራት ኢትዮጵያን ለመበቀል የተለያዩ ሴራዎችን ጠነሰሱ። ከእነዚህ ሴራዎች ውስጥ በ1898 ዓ.ም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ለንደን ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኝተው ኢትዮጵያ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ስር እንድትተዳደር መወሰናቸው አንዱ ነበር።

በ1928 ዓ.ም በእዚያ ዘመን በተፈፀሙት የወረራ ታሪኮች ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ጣልያን ግዙፍ ኃይሏን አሰልፋ ኢትዮጵያን ድጋሚ ወረረች። ከመሬት በታንክ፣ በመድፍና በመትረየስ፣ ከአየር ቦምብ በሚጥሉ እና የመርዝ ጋዝ በሚያዘንቡ አውሮፕላኖች የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨፈጨፉ። ጊዜው የዓለም መንግሥታት ማህበር



(League of Nations) ተመስርቶ የነበረበት ነበርና ኢትዮጵያ ለዚሁ ድርጅት ወረራው ተገቢ አይደለም ብላ አቤት ብትልም አጋርነት ካሳዩ ጥቂት ሀገራት ውጭ ሰሚ ማግኘት አልቻለችም።

ይሁንና የዓለም መንግሥታት ድርጅት (League of Nations) ከተመሰረተ ከአምስት ዓመታት በኋላ ጣሊያን በድጋሚ ኢትዮጵያን ለመውረር ጦርነት ጀመረች። በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና አርበኞች ሀገርን ላለማስደፈር ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል። ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የጣሊያንን ድርጊት አዲስ ለተቋቋመው የዓለም የመንግሥታት ድርጅት ለማመልከት ወደ ውጭ ሀገራት ቢሄዱም ሕግና ሉዓላዊነት በወቅቱ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ባለመሆናቸው ኢትዮጵያውያን የነጻነት ተጋድሏቸውን አጠናክረው ቀጠሉ።

የኢትዮጵያ ጦር ሀገሩን ላለማስደፈር ጠላትን በሰይፍና በጎራዴ ጭምር ተፋለመ። ነገር ግን የጣሊያን ጦር ይጠቀም የነበረው ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ድረስ እንዲዘልቅ ረዳው። ጣሊያን አዲስ አበባ ድረስ መዝለቅ ቢችልም ኢትዮጵያውያን ግን በጠላት ጦር ላይ ጥቃት መሰንዘርን አላቆሙም ነበር። በዱር በገደሉ እና በዋና ዋና ከተሞች ከፈጸሟቸው ጥቃቶች መካከል አንዱ በግራዚያኒ ላይ የተደረገው የግድያ ሙከራ ዋናው ነበር።

ግራዚያኒ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ስለጣሊያን ንጉሥ ቪክቶር ኢማኑኤል ልጅ መውለድ ደስታ ለማብሰር በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት አዳራሽ ሹማምንቱንና ሕዝቡን ሰበሰበ። በዝግጅቱ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስግዶም፣ ስምኦን አደፍርስ፣ ስብሃት ጥሩነህ እና ሌሎች ወጣቶች ቦንብ ይዘው ወደ ስብሰባው ገቡ። በተለይ አብርሃም ደቦጭ እና ሞገስ አስግዶም በኤርትራ በነበሩበት ወቅት የጣሊያን መንግሥት በኤርትራ ሕዝብ ላይ ይፈጽም የነበረውን ግፍ ያውቁ ስለነበር ከፍተኛ ቁጭት ነበረባቸው።

ወጣቶቹ ወደ አዳራሹ እንደገቡ ግራዚያኒ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ስለ አርበኞች እና ስለ ንጉሡ በንቀት ይናገር ነበር። ወጣቶቹ በግራዚያኒ የንቀት ንግግር እና በስብሰባው ውስጥ በታደመው ተሰብሳቢ ተናደዱ፤ ወደ ግራዚያኒ ቀስ ብለው በመጠጋት ሰባት ቦንቦችን በተከታታይ ወረወሩ። ተሰብሳቢው የመጀመሪያው ቦንብ ፍንዳታ የደስታ ርችት መስሎት ስለነበር አልተደናገጠም። በሁለተኛው የቦንብ ፍንዳታ ግራዚያኒ ተመትቶ ከብዙ ቦታ ላይ ቆሰለ፤ የጦር ኃይል አዛዥ የነበረው አውራሊያ ሊኦታ አይኑ ጠፉ፤ እግሩም ተቆረጠ። ሌሎች ሹማምንትም ሕይወታቸው አለፈ።

ወጣቶቹ ቦንቡን ወርውረው እና አዳራሹን አተራምሰው እንደወጡ በጓደኛቸው ከአዲስ አበባ ወደ ፍቼ በማቅናት ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ።

በአብርሃም ደቦጭ እና በሞገስ አስግዶም በተሞከረበት የግድያ ሙከራ የተበሳጨውና የፋሺስትን ጦር የሚመራው ማርሻል ሩዶልፍ ግራዚያኒ ከየካቲት 12 እስከ የካቲት 14 ድረስ ባሉት ሦስት ቀናት ከ30 ሺህ በላይ ሠላማዊ ኢትዮጵያውያንን ጨፍጭፏል። ይህንን ተከትሎም በጭፍጨፋው ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎችን ለመዘከር የካቲት 12 በብሔራዊ ደረጃ እንዲዘከር በ1934 ዓ.ም ታወጀ። በ1951 ዓ.ም ደግሞ 6 ኪሎ አካባቢ የሚገኘው እና 28 ሜትር ርዝመት እንዳለው የሚነገረው የሠማዕታት መታሰቢያ ሐውልት እንዲቆም ተደርጓል። የካቲት 12 በየአመቱ በደማቅ ሁኔታ የሚከበርና በሶስት ቀን ከ30 ሺህ በላይ ሰዎች ሕይወታችውን መስዋዕት አድርገው የሀገራቸው ክብርና ሉዓላዊነት ያስከበሩ ሰማዕታት የሚታወሱበት እንዲሁም የሚዘከሩበት ዕለት ነው። ይህንን ቀን ሰዎች በጋራ ተሰብስበው ስድስት ኪሎ የሰማዕታት ሐውልት ጋር አርበኛ የነበሩ አባቶች እና እናቶች በተገኙበት በተለያዩ ሁነቶች ይከበራል።

እንግዲህ ልጆች የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን ተብሎ የሚከበርበት ምክንያት ይህንን ይመስላል። ሀገራችን በርካታ ታሪኮች ያላት እንቁ ሀገር ናት፤ እነዚህን ታሪኮች ደግሞ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። የዛሬው መልዕክቴም ይህ ነው፤ የሀገራችሁን ታሪክ መፃሕፍትን በማንበብ ወይም ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ለማወቅ ሞክሩ እያልኩ በዚሁ ላብቃ ሳምንት በሌላ ጽሁፍ እስከምንገናኝ መልካም የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ።